# ምዕራፍ አምስት

# ማስተዋልና መቋቋም

## ማስተዋል

የሐሰት ትምህርቶች አብዛኛ ሰውነታቸውን እውኃ ውስጥ ደብቀው እንደሚንሳፈፉ ዐዞዎች ናቸው። እንዲህ ያሉ ዐዞዎች የመተንፈሻ ቀዳዳቸው ያለበትን የአፍንጫቸውን ክፍል ብቻ አውጥተው በወንዝ ላይ ይንሳፈፋሉ። አንዳንድ የዱር እንስሳት ድንጋይ መስሎአቸው መጥፊያቸው መሆኑን ሳያስተውሉ ተረማምደው ሊሻገሩበት ይሞክራሉ። አንዳንዶች በትልቅ ጉዳት ሰውነታቸውን ያተርፋሉ። ብዙዎቹ ግን ተይዘው ይበላሉ። የስሕተት ትምህርቶችን መረማመጃ መስሎአቸው የረገጡና የተነከሱ የብዙ ብዙ ናቸው።

እንዲህ ያሉት የስሕተት ትምህርቶችና ንቅናቄዎች ሲጀመሩ አደጋ ያለባቸው አይመስሉም። ሁሉን ለመሳብና ለማቀፍ የሚዘረጋ እጅና ውብ ስም ይሰጣቸዋል። የሚሰጡት ተስፋ ዓይነቱና ብዛቱ ከልክ ያለፈ ነው። ቆይተው ግን ልብን የሚሰብሩ ልምምዶችና ትምህርቶችን አቅፈው የሐሰት ትምህርቶች ብሎም የድርጅት ቅርጽ የያዙ የሐሰት ሃይማኖቶች ወይም Cult ይሆናሉ። ከልት ከቋንቋ ወይም ከመዝገበ ቃላት ትርጉም አንጻር ከማናቸውም ሃይማኖቶች እንደ አንዱ ሆኖ ሊተረጎም የሚችል ቃል ነው። አንድ ታዋቂ መዝገበ ቃላት ይህንን ቃል ሃይማኖታዊ ተግባር ወይም የአምልኮ ሥርዓት ወይም አምልኮ ያሰኘዋል። ከክርስቲያናዊ እይታ አንጻር ግን ለዚህ ከልት ለሚለው ቃል ተጨማሪ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል። ከልት ከመጽሐፍ ቅዱስ ተንደርድሮ የወጣ የተሳሳተና የተቃወሰ የአምልኮ ሥርዓት ወይም ሃይማኖታዊ ተግባር ነው። መንደርደሪያው ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በአጭሩ ከልት የሐሰት ትምህርት ነው። በሐሰት ትምህርቶች አካባቢ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ ሁለት ጸሐፊዎች በአንድነት በጻፉት መጽሐፍ ለከልት ይህን ትርጉም ሰጥተዋል፤

> ከልት በአጭሩ ሲገለጥ አንደኛ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ተጻራሪ ስነ መለኮትን የሚያስፋፋ ትምህርት ነው፤ ሁለተኛ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ላልሆነና የሰዎችን መንፈሳዊና ስነልቡናዊ ታዛዥነት ያለልክ ለሚፈልግ የሥልጣን ጥም ማጎብደድን የሚያስፋፋ ከታወቁት የዓለም ሃይማኖቶች ያልተመደበ ማናቸውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ነው።[1]





እነዚሁ ጸሐፊዎች ዶክተር ሉዊስ ጎርደን የተባሉ ሰው ይህን ቃል የተረጎሙበትን ትርጉምም አያይዘው አቅርበዋል፤ በዶክተር ጎርደን አተረጓጎም ከልት ማለት፥

> በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተመሠረተ የሚናገር ሃይማኖታዊ ቡድን ሆኖ ነገር ግን ባህርያቱን የሚገልጡት ትምህርቶቹ ከክርስትና መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር የሚቃረኑ፤ የኑሮ መለኪያቸው ከክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ጋር የሚቃረን፤ እንዲሁም የአመራር መለኪያዎቻቸው ከክርስቲያናዊ የአመራር መስፈርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው።[2]

ከሁለቱም ትርጉሞች የምንወስደው አሳብ እነዚህ ትምህርቶችና ድርጅቶች በስም ክርስቲያን ወይም ክርስቲያናዊ ሆነው በተግባር ግን ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ የስሕተት አምልኮ ሥርዓቶች ወይም የሐሰት ትምህርቶች ናቸው። እነዚህ የሐሰት ትምህርቶች በተለይ በመሪዎቹ ዘንድ የሚታወቁባቸው መለያ ነጥቦች አሉአቸው። ዋናዎቹ፥

- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ስነ መለኮት አላቸው። እነዚህ ሰዎች ስለሚናገሩት ወይም ስለሚለማመዱትና ስለሚያለማምዱት ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንደርደሪያ ያደረጓቸውን አንድ ወይም ጥቂት ጥቅሶች ሊያቀርቡ ይሞክራሉ። ሆኖም ያ ከመነሻ ጥቅስ ያለፈ አይደለም። የትምህርታቸው ጠቅላላ ይዘት መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የለውም።

- አዳዲስ መገለጦች አሉአቸው። ከእግዚአብሔር በቀጥታ፥ ወይም በሕልምና በራእይ፥ ወይም በሌላ የመገለጥ መንገድ የተገለጠላቸውን ትምህርትና በሥልጣን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልተናነሰ ትምህርት ወይም አተረጓጎም ያቀርባሉ። ከቀድሞ ጀምሮ የጸናውን የጌታንና የሐዋርያትን ትምህርት ተገለጠልን በሚሉት በአዲስ መገለጥ ይበርዙታል።

- የሚያምኑትን ማድፈንፈን ይወዳሉ። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱስ የራቀውንና አጠያያቂ የሆነውን ትምህርታቸውን በቀጥታና በግልጽ አያስተምሩትም። ሲጠየቁም ሊሸፍኑ ወይም ሊክዱ ይዳዳቸዋል። በራሳቸው ጉባኤ ወይም በጥቂት ተከታዮቻቸው ዘንድ ግን እንዲህ ያለውን ትምህርት በግልጽ ይናገሩታል።

---

[1] Ankerberg, etal. p. 347.

[2] Ibid.

• ከመጠን የዘለለ ሥልጣን ይፈልጋሉ፤ ከተራው ተከታይም እጅግ ይርቃሉ። የሥልጣናቸው ምንጭ የሚያደርጉት አንዳንዴ የሚያገኙአቸውን መገለጦች ሲሆን ሌላ ጊዜ ቀድሞም በሰዎች አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጽ ሊያደርጉ የጣሩትን መቀባታቸውን ነው። አንዳንዶቹ ከተርታው ተከታይ በጣም የራቁ ከመሆናቸው የተነሣ እነሱን ማግኘትን፥ እጃቸው እንዲጫንባቸው መመኘትን፥ ከነሱ የግል ቃል መቀበልን እንደ ብርቅ ያስደርጉታል። በውጭ ሲታዩ እነዚህ መሪዎች ታማኞች ይመስላሉ፤ ሲመረመሩ ግን ያልተረጋጉና የተረበሹ፥ ግፊታቸውና ዝንባሌያቸው ንጹሕ ያልሆነ፥ ሥልጣናቸውን ማጋራት ከቶ የማይወዱ፥ ከተጠያቂነትና ከወቀሳ በላይ አድርገው ራሳቸውን የሚመለከቱ፥ ሌላውን መጠቀሚያ የሚያደርጉ ናቸው። አንዳንዴ ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖችን ሕገኞች ራሳቸውን ነጻ ሊያስመስሉ ይሞክራሉ፤ ግን መጠፈሪያ ደንቦች አሉአቸው። ተከታዮቻቸው ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይገድቡታል። እነርሱ የሚያሸንፉበት ካልሆነ ግንኙነት እንዳይኖራቸውም ያደርጋሉ። ይህ ቤተ ሰብንም ያጠቃልላል። በመጀመሪያ በሚስቡበት ጊዜ ፍቅርን የሚያሳዩ ይመስላሉ፤ በማሞካሸትና የተጋነኑ ተአምራትን በማውራት ስለራስ የተለየ ግምት የሚያሰጥ ታሪኮችን አብዝተው ይናገራሉ፤ ያንን ተከትሎ ግን አምባገነናዊ ቁጥጥር ይመጣል። ሥልጣናቸውን ከሰዎች ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል በላይም ያደርጋሉ። በምዕራፍ ሦስት የተጠቀሰው ጂም ጆንስ አንዴ ያደረገው የዚህ ምሳሌ የሚሆን ነው። ጂም መጽሐፍ ቅዱሱን ወደ መሬት ወርውሮ፥ 'እጅግ ብዙ ሰዎች እኔን መመልከት ትተው ይህን [መጽሐፍ ቅዱስን ማለቱ ነው] ይመለከታሉ' ብሎ ነበር።[3] ከተከታዮቹ አንዱ የነበረ ሰው ሲናገርም፥ አባ አባት ብለው እንዲጠሩትና ጸሎታቸውን ወደእርሱ እንዲያቀርቡ ፎቶግራፉንም በቦርሳቸው ውስጥ አድርገው እንዲሄዱ ማለቱን ተናግሮአል።[4] እንደ እኩያ ወንድም መሰኘትን ሳይሆን 'አባታችን' ተብለው መጠራትን የመለኮታዊ ሥልጣናቸው ዣንጥላ ያደርጉታል። ማቴ. 23፥1-12 የሚያስተምረን ግን ከዚህ የተለየ ትምህርት ነው።

• 'መንፈሳዊ' ማስፈራራትና ዛቻን ይጠቀማሉ። ሊቃወሙአቸው የሚሞክሩትን ማስፈራራትና የእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍት እንደሚያገኛቸው በመናገር አንዳንዴም በመዛት ከውስጥ ያሉት እንዳይወጡ ከውጭ ባሉትም እንዳይደፈሩ ይጥራሉ። እውስጥ ያሉትን የሚያስሩባቸው ዋና ገመዶች ራሳቸው የፈጠሩአቸው

---

[3] Appel, p. 44.
[4] Enroth, p. 56





ሕግጋት ናቸው። ሃይማኖታዊ ፍርሃት በገነነባቸው ጉባኤዎች እንዲህ ያለው ማስፈራራት ትልቅ የሥልጣን እርካብ ነው።

• የቡድን ግፊትን በመጠቀም ሰዎችን መሰብሰብን ይወዳሉ። ብዙ ቁጥርን ይፈልጋሉ፤ ግን ወንጌልን በመስበክ የጠፉትን መፈለግ ሳይሆን የያዙአቸውን ጥቂቶች ወደ ሌሎቹ በመላክ፥ በተለይም ባለጠጋና ባለሥልጣን ወደሆኑት በማተኮር መስፋፋት ነው ግባቸው። ከአማኞች የልቀት ዕድገት ይልቅ በቁጥር ብዛት ያምናሉ።

ከላይ የመሪዎቹን ባህርይ በመጠኑ ነው የተመለከትነው። ትምህርቶቹም እንደመሪዎቹ የሚታወቁባቸው ባህርያት አሉአቸው። ሁለት ጸሐፊዎች ስለ ከልቶች እና ባህርያታቸው በጻፉት መጽሐፍ መለያዎቻቸው ከሆኑት መካከል የሚከተሉትን ነጥቦች በዝርዝር አስቀምጠዋል፤ እነዚህም፥ አዲስ እውነት፥ አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ የሥልጣን ምንጭ፥ በአዲስ ኪዳን ከታየውና ከታወቀው ኢየሱስ ሌላ የሆነ ኢየሱስ፥ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና ማጥላላት፥ የቃላቸውና የእምነታቸው አለመጣጣም ወይም የትምህርታቸውና የተግባራቸው ነጋጨት፥ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ስነ እግዚአብሔር ወይም ስነ ሥላሴ፥ በየጊዜው የሚለወጥ፥ የሚከለስና የሚሻሻል ስነ መለኮት፥ በአንድ ሰው ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አመራር፥ በሥራ መዳን፥ እና የሐሰት ትንቢቶች ናቸው።[5] በከልት እና በሐሊዎተ እምነት ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ ሐላውያነ እምነት *(Apologists)* ከልት የሚለውን ቃል በሁለት ስፍራ ይመድቡታል። የመጀመሪያው ከክርስትና ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ወይም የርቀት ዝምድና ብቻ ያለው ሲሆን ሁለተኛው ክርስቲያናዊ ከልት *(Cult o Christianity)* የሚሉት ነው። ይህ ከትክክለኛው ትምህርተ ክርስትና በመጀመሪያ በትንሹ አፈንግጦ ኋላም ርቆ የሄደ ነው፤ የእነዚህ ከልቶች መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ራሳቸውንም እንደ አዲስ ኪዳን መደበኛ ቤተ ክርስቲያን አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው። እነዚህ መነሻቸውና እንድርድሪታቸውን የሚያገኙት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ከዚህ አንጻር ነው ማናቸውም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ አፈንጋጭ የሆኑ ወይም ከመሐል የራ ትምህርቶች *(Aberrant teachings)* በጥብቅ መታየት ያለባቸው።

የስሕተት ትምህርት በባህርይው አሳሳች ነው። አንዱ አሳሳችነ ስሕተቱ ስውር መሆኑ ነው። ይህ ረቂቅ ባህርይ ለሰይጣን አሠራር በጣም ይመቸዋል። ብዙዎቻችን ሰይጣንን በአእምሮአች የምንመስለው ወይም ይሆናል ብለን የምናስበው እንደ እባብ

---

[5] McDowell etal., pp. 21-28.

ዘንዶ፥ አውሬ፥ እንደሚያገሳ አንበሳ ነው። በስዕል ሲገለጥም ጅራታም፥ ኮቴያም፥ ቀንዳም፥ ጥርሳም፥ ጥፍራም ተደርጎ ነው። ሰይጣን ባህርይውና ሥራው ነው እንጂ አስቀያሚ መልኩ አይደለም። ስለመልኩ ብዙ ዝርዝር ባይገኝም የተጠቀሰባቸው ቦታዎች ማስጠሎነቱን አይናገሩም። ሰይጣን የስሙ ትርጉም ጠላት ማለት ነው። በመጀመሪያ ሲፈጠር ሊጋርድ የተቀባ ኪሩብ ነበረ፤ ይህ የትልቅ ኃላፊነትና ዕድል አገልግሎት ነበረ። በፍጥረቱ ጥበብን የተሞላና የውበት ድምድማት ነበረ፤ በውስጡ በደል እስኪገኝ ድረስ በከበረ ስፍራ ከከበረ አገልግሎት ጋር ነበረ፤ ሕዝ. 28፥11-19። በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሰባቸው ስፍራዎች በሌላው የንጋት ልጅና አጥቢያ ኮከብ ተብሎአል፤ ኢሳ. 14፥12። አጥቢያ ኮከብ ማለት ንጋት ላይ ጎሕ ሲቀድ በስተምሥራቅ ደምቆ የሚታይ ኮከብ ነው። በዚህ መመሰሉ ወይም በዚህ ስም መጠራቱ አስደናቂ የሆነ ውበቱን ይገልጣል።

ሰይጣንን እንደ ብርሃን መልአክ የሚያስተውሉት ብዙዎች አይደሉም። በ2ቆሮ. 11 ጳውሎስ እንደ ቅንና ቀናተኛ አገልጋይ ለቆሮንቶስ ምዕመናን ያለውን ፍርሃት ይናገራል። እባብ ወይም ሰይጣን በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት ሌላው መጥቶ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላቸው፥ ልዩ መንፈስ ቢሰጣቸው፥ ወይም ልዩ ወንጌል ቢያቀርብላቸው እንደሚታገሡት ይናገራል። ይህም ከራሱ ጋር በማወዳደር እሱን ያልታገሡትን ወይም ያላከበሩትን ያህል እነዚያን እንደሚቀበሉ መናገሩ ነው። በዚህ አገላለጡ የእነዚህን ሰዎች እውነተኛ ማንነትም በቁጥር 12-15 እንዲህ ይገልጣል፥

> *እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ና ቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።*

ይላል። ይህ ክፍል ሰይጣን የብርሃን መልአክ መሆኑን አይናገርም፤ እርሱ ከወደቀ በኋላ የብርሃን መልአክነቱ ሥልጣን ተለይቶታል። ነገር ግን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ ለመለወጥ ችሎታ አለው። ያልሆነውን ለመሆን ሳይሆን የነበረውን ለመምሰልና ለማታለል ጥበብ አለው። አገልጋዮቹም የሰይጣን አገልጋዮች ሆነው ሳሉ የጽድቅ አገልጋዮች በመምሰል ሌላ ኢየሱስ፥ ልዩ መንፈስና ልዩ ወንጌል ማቅረብና መስጠት ይቻላቸዋል፤ እርሱም ያስችላቸዋል። ሰይጣን መስሎ ማታለል እንደሚችል አገልጋዮቹም መስለውና አስመስለው ማታለል ይችላሉ።

ከላይ እንዳየነው ሰይጣን ከፍጥረቱ ጥበብን ወይም ተንኮልን የተሞላ ነበረ። ዛሬም ተንኮለኛና ዘዴኛ ነው። በኤፌ. 6፥11 ላይ ያለው ሽንገላ የሚለው ቃል በመጀመሪያ ቃሉ ዘዴ ማለት ነው።





እስከሠራለት ድረስ ምንም ዘዴ፥ ምንም መላና ጥበብ ይጠቀማል። የሰዎችን ያልዳነ ማንነት ብቻ አይደለም የሚገለገልበት፤ የሰዎችን ባህርይም መጠቀሚያ ሊያደርገው ይችላል። ይህ ክርስቲያኖችንም የሚነካ ነው። በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መንፈስ ባልተሞሉ ክርስቲያኖች ወይም ሥጋውያን ዘንድ ትዕቢትና ንቀት፥ ጥላቻና የሥጋ ሥራዎች ሁሉ ይገኛሉ። በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ አማኞችን ሲገዛና ሲቆጣጠር የመንፈስ ፍሬ ይታይባቸዋል፤ በባህርያቸውም ክርስቶስን መምሰላቸው ይገለጣል። ለባህርይ መቀረጽ ሁለቱም፥ ለመንፈስ ቅዱስ መገዛትም፥ በእግዚአብሔር ቃል መሞላትም አስፈላጊዎች ናቸው ኤፌ. 5፥18-20፤ ቆላ. 3፥15-17። እግዚአብሔር ከልጆቹ የሚጠብቀው ባህርይ የክርስቶስ ባህርይ ነው። ይህም አስቀድሞ ያወደው ዕቅድና ውሳኔ ነው። 'ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰኖአልና' ሮሜ. 8፥29። ይህ የልጁን መልክ መምሰል ሰፊና ጥልቅ፥ የሕይወትን ዘመን ሁሉ ተጋድሎ የሚጠይቅና በየቀኑ ወደ ፍጹምነት የማደግ ሂደት ነው። በመከራና በሚፈትኑ ነገሮች ውስጥ በእርሱ እየታመኑ መውጣትን፥ በታማኝነት ጸንቶ ማገልገልን፥ እንደ ጎርፍ ጎርፈው መጥተው በሚሄዱ ነገሮች ያለመወሰድን የሚጨምር ነው። ክርስቶስን መምሰል እርሱን የመከተል ጎዳና ነው፥ የመስቀልም መንገድ ነው። አዳዲስ ትምህርቶችንና ዘመናዊ መንፈሳዊ ንቅናቄዎችን በምናይበት ጊዜ ከቀደመውና ዋጋ ከሚጠይቀው የመስቀል ጎዳና ምን ያህል ያፈነገጡ መሆናቸውም ከቃሉ ትምህርት ልንረዳ ይገባናል። ሰይጣን ከእነዚህ ዋጋ የሚያስከፍሉ ነገሮች መራቅን አሸብርቆ ሊያቀርብልን ይችላል።

በክርስትና ሕይወት ግባችን 'የልጁን መልክ እንዲመስሉ' ከተባለው ክርስቶስን ከመምሰል በታች የሆነ ነገር መሆን የለበትም። በካሪዝማዊ ንቅናቄ በጣም የሚተኮርበት አንድ ልምምድ አለ። ያ እስኪገኝ የማይፈነቀል ድንጋይ፥ የማይቆፈር ጉድጓድ የለም። ያ ከተገኘ በኋላ ግን በዚያ ልምምድ ዙሪያ ከሚሽከረከረው በቀር ሌላው ዕድገት ያቆማል። ለብዙዎች ያ ልምምድ ልሳን ነው። ሰዎች በልሳኖች ለመናገር ያደረጓቸውን ብዙ እንግዳ የሆኑ ነገሮች ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ይህን ልምምድ ያላገኙት በኀዘን ሲመቱና በቀረው ዘመናቸው ሌላውን ሁሉ ትተው እሱን ብቻ ለማግኘት ሲጸልዩ፥ የተለማመዱት ደግሞ አንድ ትልቅ የእምነት እርከን እንደተሻገሩ ይቆጥሩታል። ከተራ ወይም መለስተኛ ክርስትና ወደ ዋናና የመጨረሻ ደረጃ እንደተሻገሩ ይመስላቸዋል። በተራቸው ሌላውን እንደ ጎዶሎ ክርስቲያን መቁጠር ይጀምራሉ። ከዚህ ጋር የሚያሳዝነው ያ ልምምድ ጣራቸው ይሆንና በዚያ መናገር ብቻ እንጂ ከዚያ በላይ ማደግ ይቀራል።

በአካላዊና ስነ ልቡናዊ ዕድገት ውስጥ ከወላጆች ከሚወረስ የዘር የሆነ ወይም በተለያዩ ድንገተኛና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ምክንያት የሰዎች አካላዊና ልቡናዊ ዕድገት ሊዛባ እንደሚችል ይታወቃል። አንዳንድ ሰዎች በዕድሜያቸው እያደጉ በአካላቸው አያድጉም። አንዳንዶች ደግሞ ዕድሜያቸው እየሄደም በአእምሮ ወይም በልቡናዊ ብስለታቸው ግን አንድ ደረጃቸው ላይ ተተክለው ይቀራሉ። በተለይ ይህንን የአእምሮና የልቡና እድገት መቆም የዕድገታዊ ስነ ልቡና ጠበብት Fixation ይሉታል። በአንድ የእንጭጭነት ደረጃ ላይ ቆሞ ወይም ተቆልፎ መቅረት ማለት ነው። በመንፈሳዊውም ዕድገት እንዲህ የመሰለ ነገር ሊኖር ይችላል። አዲስ ኪዳን፥ በተለይም የመልእክቶች መጻሕፍት ክርስቲያኖች እንዲያድጉ እጅግ በብዙ ያሳስባሉ። ጳውሎስ በ1ቆሮ. 3፥1-3 ላይ የቆሮንቶስን ምዕመናን በመንፈሳዊነት ፈንታ ሥጋውያን ክርስቲያኖች በመሆናቸው ይወቅሳቸዋል። ወተት እንደጋታቸው ይና ገራቸዋል። የዕብራውያን መልእክት ተቀባዮችም በእምነታቸው አድገው አስተማሪዎች ሊሆኑ በሚጠበቅባቸው ጊዜ ገና የክርስትናን የመጀመሪያ ትምህርት ሊማሩ ይፈልጉ ነበር፤ ዕብ. 5፥11-14። ስለዚህ በክርስትና ሕይወትም ውስጥ አንድ ቦታ ቆሞ መቅረት፥ ወይም ባሉበት መሄድ አለ። ከላይ እንዳየነውም ሳያድጉ አድጎ ጣራ ነክቶ መቆምም አለ። አንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኔ መጋቢ ሲሰብክ አባቱ ቢስኪሌት እንዲገዛለት ስለሚጨቀጭቀው ስለ አንድ ትንሽ ልጅ ምሳሌ ሰጥቶ ነበር። ይህ ትንሽ ልጅ ቢስኪሌቱ መቼ እንደሚገዛለት አረጋግጦ ማወቅ ፈለገና አባቱን፥ 'ታዲያ መቼ ነው የሚገዛልኝ?' ብሎ ጠየቀ። አባቱም ለልጁ ትልቅ ሲሆን እንደሚገዛለት ለማስረዳት በሚገባው መንገድ፥ 'አልጋህ ላይ ስትተኛ ከጫፍ እስከጫፍ ከደረስክ አድገሃል ማለት ነውና ያኔ ይገዛልሃል' አለው። ከጥቂት ቀናት በኋላ አባትየው ከሄደበት መጥቶ ወደቤት እንደገባ ትንሹ ልጅ፥ 'አድጌአለሁ በቃ ቢስኪሌቴ ይገዛልኝ!' አለው። አባቱም እንዳላደገ ሊያስረዳው ሲሞክር ልጁ፥ 'አይደለም አድጌአለሁ፤ ና ላሳይህ' አለና ይዞት ወደ አልጋው ሄዶ በመጋደም ከጫፍ እስከጫፍ ደርሶ አረጋገጠለት። እውነትም ልጁ ከጫፍ እስከጫፍ ደርሷል። ግን የተጋደመው ከራስጌ ወደ ግርጌ ሳይሆን ከጎን ወደ ጎን ነበር።

ልጁ ለራሱ በመሰለው መንገድ አድጎ ከጫፍ እጫፍ ደርሶአል። በእውነቱ ግን የጥቂት ቀናት ዕድገት ብቻ ነው ያደገው። አካላዊ ዕድገት ውስብስብ ሂደት ነው። አእምሮአዊም፥ ልቡናዊም፥ ማኅበራዊም ዕድገቶች እንደዚያ ናቸው። መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ዕድገትም ከዚህ የተለየ አይደለም። እርግጥ የዕድገት ልቀት ከሰው ወደ ሰው ይለያያል። እንደመሰጠታችንና እንደትጋታችን መጠን እመር ሊልና ሊፈጥን ይችላል። እንደስንፍና





ችንም ሊተጓጎል ወይም ሊቆምም ይችላል። በመሠረቱ ግን ዕድገት በጊዜ ውስጥ የሚታይ ውጤት ነው።

የአንዳንድ አገልጋዮች ስሕተት የቅንነትና የየዋኅነት ሊሆን ይችላል። በምዕራፍ አንድ ከጥያቄዎቹ በአንዱ እንደተመለሰው ከስሕተት አስተማሪዎች ጀርባ የየዋኅነት ወይም ያለማወቅ ስሕተትም ሊኖር ይችላል። ያለማወቅም ሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቅ ነው። አንድ ሰው ዝም ብሎ ቢወዘፍ መሳሳቱ አይታወቅም፤ በዚያው ልክ አለመሳሳቱም አይታወቅም። ሲንቀሳቀስ ግን አቅጣጫው ይታወቃል። በእንቅስቃሴ ውስጥ መሳሳት ሊኖር ይችላል። አንድ መሥሪያ ቤት አንድ ጊዜ ሾፌር ለመቅጠር ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ አወጣ። ከመመዘኛዎቹ መካከል በግልጽ እንደ ዋና የተጠቀሱት ሁለቱ የረጅም ዘመን የሥራ ልምድና በነዚህም ጊዜያት አደጋ ያለማድረስ ናቸው። ብዙ ተወዳዳሪዎች ቀርበው የጽሑፍ ፈተና ወሰዱ። አንዳንዱ በአጭር ጊዜ የሥራ ልምድ፥ ብዙዎቹ ደግሞ ከቋሚም ከተንቀሳቃችም ነገሮች ጋር በተደረጉ ግጭቶች ፈተናውን ወደቁ። አንድ ሰው ብቻ በ25 ዓመታት ልምድና ምንም አደጋ ባለማድረስ ፈተናውን አለፈ። የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊም ይህን ሰው የጽሑፍ ፈተናውን ማለፉን አድንቆ ነገረውና ለቃል ፈተና ወደ ቢሮው ይዞት ገባ። 'ለመሆኑ በነዚህ 25 ዓመታት ምን ምን ዓይነት መኪናዎችን ነበር የነዳኸው?' ብሎ ጠየቀው። ሾፌሩም፥ 'ጌታዬ፥ ካያ አምስቱንም ዓመት ዳምጠው የሚባለውን ዳማጭ መኪና ነበር ሳንከባልል የኖርኩት' ብሎ አሳረፈው። በዳምጠው የሚዳመጥ ሰው መቼም ሊኖር አይችልም። ሌሎቹ ግን ፍጥነትም አደጋም ይኖራቸዋል። በችኮላ ውጤት ለማግኘትና አንዳንዴም በወጣትነት ስሜት አንዳንዶች ሊስቱና አደጋ ሊፈጥሩ ይችላሉ። አደጋው መልካም ባይሆንም ሰዎቹ መታረም ቢችሉ ውብ ነገር ነው። የአገልጋዮች አደጋዎች ብዙ መነሾዎች ቃሉን እንደሚገባ ያለማወቅ ወይም ያለማጥናት ነው።

የሰይጣንን ዘዴና ኃይሉን አለማወቅና፥ በአንጻሩም የእግዚአብሔርንም ኃይልና ቃሉንም አለማወቅ ለስሕተት አሠራር ሊዳርጉን ይችላሉ። በማቴ. 22፥29 ላይ ጌታ ሰዱቃውያንን፥ 'መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ' አላቸው። እነዚህ ትንሣኤ ሙታንን የሚክዱ ሰዱቃውያን ናቸው። በመጀመሪያ ጥያቄአቸው የፌዝ ነው የሚመስለው፤ ምክንያቱም በትንሣኤ ስለማያምኑ። በትንሣኤ ሙታን የማያምኑ ከሆኑ ከትንሣኤ በኋላ ስለሚሆነው መጠየቅ አልነበረባቸውም። ስሕተታቸው ሁለቱም፥ ማለትም፥ ቃሉንም ኃይሉንም አለማወቅ ነበር። መጻሕፍት ስለ ትንሣኤ ይናገራሉ፤ ያንን አላስተዋሉም፤ ደግሞም የእግዚአብሔር ኃይል ሙታንን ማስነሣት ይችላል፤

ይህንንም አላመኑም። ዛሬም የዚህ ሚዛን፥ ማለት፥ የእግዚአብሔር ቃልና ኃይል በጤና መጠበቅ አለበት።

አንዳንድ ሰዎችን ወደ ስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች ከሚስቡአቸው ነገሮች መካከል አንዱ የጓደኞች ጉትጎታና ጉተታ፥ ግፊትና ጫና ነው። ተቀባይነትን ለማግኘት ብቻ ሲባል ከእነርሱ እንደ አንዱ ለመሆን ያልፈለጉትንና እርግጠኛ ያልሆኑበትን ነገር የማድረግ ሁኔታ አለ። ስለዚህ በምንም ዓይነት ግንኙነት ውስጥ ይህ ግፊትና ስበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወዳልሆነ ትምህርትና ልምምድ የሚመራ ከመሰለ መጸለይና ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር መወያየት ጠቃሚና ጠባቂ ሊሆን ይችላል።

የስሕተት ትምህርቶችን ከውጪ እንደሚመጡ ብቻ በማሰብ ከውስጥ ለሚነሡ ስሕተቶች ትጥቅን ማላላት ለመወሰድ ማንቀላፋት ነው። የሐሰተኛ ትምህርቶች ታሪክ የሚያስተምረን ጉልህ ነገር እጅግ አብዛኞቹ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ መውጣታቸውን ነው። የእነዚህ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ወንጌላትም መልእክቶችም የሚያስጠነቅቁን ይህን ነው። ዙሪያችንን የሚዞረን አንበሳ ተኝተን እንዳያገኘን ልንጠነቀቅ ይገባናል። ናይሮቢ በሚገኝ አንድ መካነ መቃብር የአንድ አገር ጎብኚ መቃብርም ይገኛል። በመቃብሩ ድንጋይ ላይ፥ 'ቻርልስ ራይል፤ በኪማ ጣቢያ ተኝቶ ሳለ በአንበሳ ተገድሎ ሞተ' የሚል ተጽፎአል። ተኝቶ ሳለ በአንበሳ ተገደለ። የስሕተት ትምህርቶችና አስተማሪዎች ከውጪም እንደሚገቡ ከውስጥም እንደሚነሱ ማስተዋል ተገቢ ነው። ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች አስጠርቶ ምክርና ትንቢታዊ ማሳሰቢያ ሲሰጣቸው ይህንን ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፥ 'ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።' ሐዋ. 20፥29-30። ስለሁለቱም ዓይነት ሰዎች ይናገራል፤ ነጣቂ የሆኑ ጨካኞች ተኵላዎች ይገቡባቸዋል፤ በእነርሱም መካከል አሳቾች ይነሣሉ።

የስሕተት አስተማሪዎች ተከታዮቻቸው ከቶም እንዲጠራጠሩአቸው አይፈልጉም። ራሳቸውንም፥ ትምህርታቸውንም፥ ታሪካቸውንም ሁሉ በእምነት እና ያለጥርጥር እንዲቀበሉ ያደርጋሉ። ማመን እንጂ መጠራጠር አፍራሽና አሉታዊ ነገር መሆኑን አጽንተው ያስተምራሉ። ተጠራጣሪ መሰኘት ለስሜት ጥሩ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም ማናቸውንም መሪዎች በተጨፈኑ ዐይኖች ከመከተል ይልቅ በተከፈቱ ዐይኖች መመርመርና ካስፈለገ ዋጋ መክፈል ይሻላል። ጌታ በማቴ. 7፥15-20 እንዳስተማረው የነዚህን ሰዎች ትምህርታቸውን ብቻ ሳይሆን ከዚህም ባሻገር ፍሬያቸውንም ማየት ተገቢ ነው። እኒህ ካልገጠሙ እነዚህ አደገኛ መንፈሳዊ መሪዎች ናቸው። አደገኛና መንፈሳዊ የሚሉት ቅጽሎች የማይጎዳኙ ቢመስሉም ቃላቱ እነዚህን ሰዎች የሚገልጡ ናቸው።





አደገኛነታቸው ግልጽ ነው፤ መንፈሳዊነታቸው ደግሞ መልካቸው ነው። የበግ ለምድ እንደለበሱ ተኵላዎች ማለት ነው። በአንድ ስለ አደገኛ መንፈሳዊ ቡድኖች (*Dangerous Religious Groups* ወይም በምኅጻረ ቃል *DRG* ይባላል) መሪዎች የተጻፈ ሰፋ ያለ መጣጥፍ ላይ የመሪዎቹን ባህርያት የሚያሳዩ 15 አስረጅ መጠይቆች ሰፍረዋል። እነዚህ ነጥቦች እንዲህ ያሉትን ሰዎች ወይም መሪዎች ማንነት ገልጠው ስለሚያሳዩ እንዳሉ አቅርቤአቸዋለሁ፤[6]

1፥ እነዚህ መሪዎች በትህትናና በአክብሮት ወይስ በንቀትና በትዕቢት የተሞሉ ናቸው? 2ቆሮ. 10፥18።

2፥ ገሮች ናቸው ወይስ ኃይለኞች? 2ጢሞ. 2፥24-26።

3፥ ሥልጣን ላላቸው የሚወድቸውም ሆኑ የማይወዷቸውን ሁሉ፥ ማለትም፥ ለጌታ፥ ለወላጆች፥ ለመንግሥትና፥ ለሰይጣን ጭምር ተገቢ አክብሮት ወይም አመለካከት አላቸው? 2ጴጥ. 2፥10-12፤ ይሁ. 8-10።

4፥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አክብሮት አላቸው? 1ቆሮ. 3፥1-9።

5፥ የሚከተሉአቸውን ሰዎችስ በግላቸው እንዲያስተውሉ፥ እንዲያድጉ፥ እንዲበስሉ ያደርጉአቸዋል ወይስ የነሱ ጥገኛና ታዛዥ ሆነው እንዲኖሩ ያደርጋሉ ሐዋ. 17፥11፤ ኤፌ. 4፥11-16።

6፥ የአባሎቻቸውን ገንዘብ ይበዘብዛሉ? 1ጴጥ. 5፥2፤ 2ጴጥ. 2፥3።

7፥ በትዳራቸውስ ንጹሖች ናቸው ወይስ ለሐሜት የተጋለጡ ናቸው? 2ጴጥ. 2፥14።

8፥ ስለ ኃጢአትስ ፍቅር በተሞላ ድፍረት እውነቱን ይናገራሉ ወይስ ቡድናቸው ሊሰማ የሚፈልገውን ነገር ብቻ ይናገራሉ? 2ጢሞ. 4፥3-4።

9፥ ለቡድናቸው ወይም ለማኅበሩ ሲሉ የራሳቸውን ፍላጎት መስዋዕት ያደርጋሉ ወይስ እንደ ንጉሥ ሆነው በሰዎች ትከሻ ላይ ይኖራሉ? ፊል. 2፥3-4።

10፥ የቡድናቸውን ወይም የተከታዮቻቸውን አትኩረትና ተከታይነት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያስደርጋሉ ወይስ አትኩረትን ወደራሳቸው ይስባሉ? ሐዋ. 20፥28-31፤ 3ዮሐ. 9-10።

---

[6] De Hann II, pp.9-10

11፥ ሲመሩስ አመራራቸው የራሳቸውን ታላቅነት በማግዘፍ ነው ወይስ እውነትን በማሳወቅ፥ በማበረታታትና በምሳሌነት ነው? 1ጴጥ. 5፥1-4።

12፥ እንደ ወንድም ወይም እኩያ እንዲታዩ ፈቃደኞች ናቸው? ማቴ. 23፥8-12።

13፥ ያ ቡድን የሚወደደው ወይም የሚጠላው በክርስቶስ ላይ ባለው የግል እምነትና ታዛዥነት ነው ወይስ በመሪው ወይም ጀማሪው ትምህርትና አተረጓጎም የተነሣ ነው? 1ጢሞ. 1፥37።

14፥ አባላትን የሚይዙት ወይም የሚጠብቁት በፍቅር፥ በምሳሌነትና በትምህርት ነው ወይስ ቡድኑን ትተው እንዳይሄዱ በማስፈራራት? ገላ. 2፥11-21።

15፥ የመንፈሳዊ መሪነትን መስፈርት ያሟላሉ ወይስ የመሪነት ችሎታ ከአጠያያቂ ባህርይ ጋር ያላቸው ሰዎች ናቸው? 1ጢሞ. 3፥1-7።

እኒህ ከላይ ያየናቸው ነጥቦች የትክክለኛና የስሕተት ትምህርት መሪዎችን ለማነጻጸር ዓይነተኛ መስፈርት ናቸው። ከዚሁ አያይዞ ጸሐፊው አደገኛ ሃይማኖታዊ ቡድኖች የሚላቸውን የስሕተት ትምህርት መሪዎች አሳሳች ባህርያት ጨምሮ ይዘረዝራል። አንዱ ነጥብ እነዚህ ሰዎች ከነባር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጋር የተጣሉና የሰለቻቸው ሆነው ቤተ ክርስቲያንን ወደቀድሞ ስፍራዋ ለመመለስ ጌታ በዚህ ዘመን የለውጥ ሐዋርያ አድርጎ ያስነሣቸው በመሆናቸው አሳብ የተሞሉ ናቸው። የሌሎችን ቤተ ክርስቲያኖች እንደ ሙት፥ እንደ በድን፥ እንደ ሰንበቴ፥ እንደ ማኀበር፥ እንደ ዕድር የራሳቸውን እንደ ብቸኛዋ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን አድርገው ያቀርባሉ። እንዲህ ሌላውን በማጥላላትና የራስን በማሞካሸት ሲናገሩ በኖሩባት ቤተ ክርስቲያን ቅሬታ ያደበበባቸው ሰዎች በቀላሉ ሊሳቡላቸው ይችላሉ።

እነዚህ የተሳቡና የተከተሉአቸውን ሰዎች እውነትን ያገኟት እነርሱ ብቻ መሆናቸው ይነገራቸዋል። ስለዚህ ለዚህ እውነት ዋጋ መክፈል እንዳለባቸው፥ ይህን እውነት ለማዳረስም መስዋዕት እንዲከፍሉ ይደረጋሉ። ሌሎች ስለእነርሱ የሚሉትን እንዳይሰሙና የጻፉትን እንዳያነቡ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ቀድሞ የሚያውቁትን፥ የኖሩበትን፥ የተማሩትን እንዲጥሉ ይደረጋሉ፤ በአዲስ ልምምድም ይጠመቃሉ። መሪዎች አባትና ሙሉ ተቆጣጣሪ ተከታዮችም ልጅና ጥገኛ ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ቢጠናና ቢሰበክም ጥናቱም፥ ስብከቱም፥ ትምህርቱም በመሪው የአተረጓጎም ስልት የተቀነባበረና የተቀናጀ ነው። የሚያዩትና ተስፋ የሚያደርጉት እንደ ቀስተ ደመና ባለብዙ ኅብር የሆነ ውብና ያማረ ነገር ነው፤ ግን፥ እንደቀስተ ደመናው ደርሰው





የማይጨብጡት ነው። እንዲህ ያለው ነገር ልቡናን የሚያሳውር ተስፋ ነው።

በቅርቡ አላስካ በሚባለው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ በሚገኝ አንድ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ አንድ ድብ ሞቶ ተገኘ። ወደ አካባቢው መጥተው የነበሩ ጎብኝዎች ድንኳናቸውን ጥለው ከሰነበቱና ነቅለው ከሄዱ በኋላ ድቡ ወደ ስፍራው መጥቶ የተጣሉ ቆሻሻ ነገሮችን ሲለቃቅም ይቆያል። እንዲያ እያደረገ አንድ ስምንት ኪሎ የሚይዝ የቡና ታኒካ ያገኝና አንገቱን ከትቶ ያገኘውን ነገር መላስ ይጀምራል። ቀና ሲል ግን ታኒካውም አብሮት ተነሣ። ሊያራግፍና ጭንቅላቱን ለማውጣት ቢሞክር እንቢ አለው። ቢሮጥ፥ ቢዘል፥ እንጣጥ ቢል፥ ቢንፈራገጥ ሊወጣለት አልቻለም። በድንጋጤና ማየት ካለመቻሉ የተነሣ እየዞረ፥ እየዞረ፥ እየዞረ ደክሞት ሞተ። ድቡን ያገኘው የደን ጠባቂ ፓይለት እንደገመተው ድቡ ከመሞቱ በፊት ወደ 900 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዟል። እልስ ብሎ ተላሰ። አሳች ትምህርቶችም የሚላስ ነገር ሰጥተው በቀላሉ አሳውረው የሚወስዱ ናቸው።

ስሕተቶች ቀላልና ትንሽ ቢመስሉም አደጋቸውን ወይም መዘዛቸውን ግን እንደቀላል አንመልከት። አይጦችን ለመግደል የተሠራው የአይጥ መርዝ ሙሉ በሙሉ መርዝ አይደለም። እንዲያውም 98% እህል ነው። 2% ብቻ ነው መርዝ። ግን አይጦቹ ብዙው ክፍል የሆነውን እህሉን በልተው በመወፈርና በመኖር ፈንታ ከበሉት ውስጥ በጣም ትንሽ የሆነው ቅመም ይገድላቸዋል። ገዳዩ ያ ነው። የስሕተት ትምህርቶችን ገዳዮች፥ አጥፊዎች የሚያደርጋቸው የስሕተቶቹ ኃይለኛነት ነው።

# አስጠንቃቂዎች እንሁን

አደጋ ሳይመጣ መጣ ብሎ መጮህ አስበርጋጊነት ሊሆን ይችላል፤ ሊመጣ እንደሚችል በማሰብ ወይም በዙሪያ ከሚታዩት ነገሮች ተነሥቶ ማስጠንቀቅ ግን አሸባሪነት አይደለም። በሁለተኛው ዓለም ጦርነት መጨረሻ ላይ በነበረው የአሜሪካና የጃፓን ጦርነት ታሪክ ጎልተው የሚታወቁት በአሜሪካ የደረሰው የፐርል ሐርበር ፍጅትና በጃፓን የሆነው የአቶሚክ ቦምብ ፍንዳታ ነው። በፐርል ሐርበር የሆነው ይህ ነበር።

ፐርል ሐርበር በፓሲፊክ ውቅያኖስ ከምትገኘው ሐዋይኢ ከምትባለው የአሜሪካ ደሴት ግዛት ያለች ሰርጥ ናት። እንደ ፈረንጆች ቆጠራ እሁድ ዲሴምበር 7 ቀን 1941 ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት ጃፓኖች ያልታሰበና ያልተጠበቀ ወረራ ፈጸሙ። በጃፓን በኩል በተደረገው በዚህ 353 የጦር አውሮፕላኖች የተሳተፉበት ወረራ በሁለት ሰዓቶች ውስጥ አሜሪካ 6 የጦር አውሮፕላን

ማረፊያዎች፥ 8 የጦር አውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦች፥ ጥቂት ብቻ ሲተርፉ 183 ተዋጊ አውሮፕላኖች፥ ወደ 3ሺህ የሚጠጉ የባህር ኃይልና የምድር ጦር ወታደሮችን በሞት ስታጣ 1153 ወታደሮች ቆስለዋል። የጃፓን የዚህ ጊዜ አብራሪ ተዋጊዎች 'ካሚካዚ' የሚባሉት ፓይለቶች ናቸው። ካሚካዚ ማለት ሞቶ ገዳይ ወይም አጥፍቶ ጠፊ እንደማለት ነው። እነዚህ አብራሪዎች በአውሮፕላኖቻቸው ትላልቅ ፈንጂዎችን ጭነው በመብረር በዒላማቸው ላይ በመጣል ሳይሆን ላለመሳት አብረው በመላተም የሚያጠፉና እነሱም በዚያው የሚሞቱ አብራሪዎች ናቸው። ጃፓኖች በተለምዶአዊ ጦርነት መርታት ስላልቻሉ ያልተለመደ ጦርነት መክፈታቸው ነበር።

ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ጠዋት ልክ በ1 ሰዓት ላይ ከ300 ያህል ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በፓሲፊክ ውቅያኖስ ላይ የነበሩ የአሜሪካ ራዳሮች በአንዱ ይሠሩ የነበሩት የአየር ተቆጣጣሪዎች በመሣሪያቸው ላይ ነጠብጣብ የመሳሰሉ ነገሮች ማየት ጀመሩ። ያዩትም የራዳር ኦፕሬተሮች ቀኑ እሁድ በመሆኑና ዋናዎቹ አዛዦች በቅርብ ስላልነበሩ በቅርብ ላገኙት ወጣት አዛዥ ነገሩት። እርሱም ከካሊፎርኒያ የሚመጡ የራሳቸው አውሮፕላኖች እንደሆኑ በመገመት፥ "አትጨነቁ፥ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም" የሚል አረጋጊና የትእዛዝ ቃል ሰጠ። ከእልቂቱ በኋላም ተጠያቂ የሆኑት ዋና አዛዦች ሪር አድሚራል ኪመር እና ጀነራል ሾርት የተባሉ ሰዎች የውሳኔ ስሕተት በመፈጸማቸው ወዲያው ከአገልግሎት ተገልለዋል። ከታዩበት እስከደበደቡበት እስከ ሁለት ሰዓት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ አውሮፕላኖቹን በሙሉ ማስነሣትና አውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦቹንም ለውጊያ ማዘጋጀት፥ ሁሉንም ከአደጋ ማዳን ሲቻል፥ "አትጨነቁ" በሚል የቸልታ ትእዛዝ ያ ሁሉ መሳሪያ ወደመ፤ ያ ሁሉ ሠራዊትም በከንቱ አለቀ። በቸልታ ትእዛዝ ድንገተኛና ትልቅ ውድመት ደረሰባቸው። አደጋ ከኖረ የማስጠንቀቂያ ቸልታ ውጤት እልቂት ነው።

አደጋዎች ከመፈጸማቸው በፊት ማስጠንቀቅና መጠንቀቅ ትልቅ ነገር ነው። ይህ ሳይሆንና የጉዳት ሰለባ ከተሆነ በኋላም ቢሆን አስጠንቃቂነት ሊኖር ይችላል። አንዱ በተጎዳበት መንገድ ሌላው ከመሄድ መጠንቀቅ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የማስጠንቀቁ ኃላፊነት መሆን ያለበት የተጎጂዎቹም ጭምር ነው። ለአካል፥ ለጤንነት፥ ለንብረት፥ ለአእምሮ፥ ለስሜት፥ ለእምነት ጉዳት የተዳረጉ ሰዎች የማስጠንቀቂያ ድምጻቸው ካሉበት መሰማት አለበት እንጂ እነርሱ ባለፉበት ጎዳና ሌሎቹም እየሄዱ ራሳቸው ተጎድተው እንዲማሩ በማሰብ ዝም ማለት የለባቸውም።

መሪ አገልጋዮች ሊሳሳቱ ይችላሉ። ከስሕተት ትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ ብቻ ሳይሆን በአያሌ ሌሎች ሁኔታዎች የእግዚአብሐር ሰዎች ይሳሳታሉ። በቅዱስ ቃሉና በራሱ





በእግዚአብሔር መንፈስ ካልተመሩ ሊስቱ፥ ሊያስቱም ይችላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ መሪዎች መሳሳታቸው ለትምህርታችን ተጽፎልናል። የስሕተቶቻቸው ምንጮችም ሁሌም አንድ ዓይነት አይደሉም። ጥቂቶቹን ለምሳሌ እናጢን።

- ከፍርሃት የተነሣ የተሳሳቱ ነበሩ። ፍርሃት ጠንካራ ስሜት ነው። የሚከተል ችግርን አይቶ መፍራት የተሳሳተ እርምጃን ያራምዳል። አብርሃም፥ ዘፍ. 12፤ ይስሐቅ፥ ዘፍ. 26፤ ኤልያስ፥ 1ነገ. 19።

- ለሰዎች አሳብ በማለት፥ ሌሎችን ለማስደሰትና በፊታቸው ሞገስን ለማግኘት በማሰብ ያልተገባውን ለማድረግ መሞከር ወደ ስሕተት ይመራል፤ ሳኦል ይህን አደረገ፤ 1ሳሙ. 13 እና 15።

- ከግድ የለሽነትና ከሥጋዊነት የተነሣ ስሕተት ሊመጣ ይችላል። መሪዎችም ሰዎችና ሥጋ ለባሾች ናቸውና ከዚህ ስሕተት የተጠበቁ ፍጡራን አይደሉም። እንደ መሪነታቸው መጠን ግን ስሕተቱ ከእነርሱም አልፎ ሌሎችንም ሊጎዳ ይችላልና ጥንቃቄው ይበልጥ ሊሆን ያሻል። ሶምሶን፥ መሳ. 14-16፤ ዳዊት፥ 2ሳሙ. 11፤ ጴጥሮስ፥ ገላ. 2፥11-14፤ ዲዮጥራጢስ፥ 3ዮሐ. 9-10።

- ከሥጋዊ ቅንዓት የተነሣ። ይህ አደገኛ ስሜት ነው። እንደ አውሬ ሊያደርግ የሚችልም ውስጣዊ ኃይል አለው። ሳኦል የዚህ ምሳሌ ነው፤ 1ሳሙ. 18። ሳኦል ከዘመኑ ብዙውን ያጠፋው መንግሥትን በማጠንከር፥ አገርን በማልማት፥ ሕዝብን በማደስ፥ ድንበርን በማስፋት ሳይሆን አንድ ዳዊት በማሳደድ ነበር።

- ከቸልታ፥ ከስንፍናና ካለማስተዋል። እንደ መሪ ቦታን ያለማወቅና እንደ መሪ መጠን እግዚአብሔርን ያለማማከር ትልቅና የማይቀለበስ ስሕተት ያስፈጽማል። አሮን፥ ዘጸ. 32፥ 1-6፤ ኢያሱ፥ ኢያ. 9፥3-15።

- የሰይጣንን አሳብ ባለማስተዋል በማገልገል መሪዎች ሊስቱ ይችላሉ። ዳዊት፥ 1ዜና. 21፤ ጴጥሮስ፥ ማቴ. 16፥ 21-23።

ስሕተትን ማስተዋልና አስተውሎም መመለስ ድንቅ ልምምድ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ በብዙ አቅጣጫ ችኩል ሰው እንደነበር በወንጌላት ይስተዋላል። የተረጋጋና ቀስ ብሎ የሚሄድ ዳምጠው እንደሚነዳው ሾፌር ያለ ሰው አይደለም። ስለዚህም ይሳሳታል። ሆኖም ምልስ ሰውም ነበረ። ጌታውን እስኪክድ እንኳ ደርሶ ነበር። ከካደ በኋላ እንኳ በመራራ ልቅሶ ተመለሰ። ጌታም መልሶ ሾመው እንጂ እንደማይረባ ሰው አንገዋልሎ አልጣለውም። ዳዊትም

ይህን የመሰለ ሰው ነበር። መተላለፉን ራሱ አውቆ ሊመለስ የሚጥር፥ መዝ. 19፥12-14፤ ሲያሳውቁትም በእውነት የሚመለስ ሰው ነበር፥ መዝ. 51 እና 2ሳሙ. 12። በአንጻሩ ደግሞ ሳኦል ስሕተቱ ሲነገረው ሰበብ የሚሰጥና እልከኛ ሰው ነበር፤ ለምሳሌ 1ሳሙ. 15። ስለመታረምና ተግሳጽን ስለመቀበል የእግዚአብሔር ቅአል ምክር ብዙ ነው። ምሳ. 12፥1፤ 13፥18፤ 15፥10-12 እና 32፤ 17፥10፤ 10፥25-27 ወዘተ። ስሕተት ሊኖር ይችላል፤ መመለስም መኖር አለበት። ስተው የተመለሱም ለሌሎች የማስጠንቀቅ ኃላፊነት አለባቸው።

በፈረንጆች አቆጣጠር በ1973 በሳን በርናርዲኖ፥ ካሊፎርኒያ ነዋሪ የሆኑ ሎሬንስ እና አሊስ ፓርከር የተባሉ ባልና ሚስት ክስ ተመስርቶባቸው የ25 ዓመት ጽኑ እስራት ተበይኖባቸው ወደ እስር ቤት ገቡ። መነሾው እንዲህ ነበር፤ ዌስሊ የተባለ የ11 ዓመት ልጃቸው በስኳር በሽታ ይታመማል። እነርሱም የሕክምና መፍትሔ በመፈለግ ላይ ሳሉ አንድ የቃል እምነት ሰባኪና የፈውስ ስጦታ አለኝ የሚል ሰው ልጁ መፈወሱንና እነርሱም እምነታቸውን እያጸኑ ሕክምናውን እንዲያቆሙ ይነግራቸዋል። አያይዞም አሉታዊ ወይም አፍራሽ ንግግር እንዳይናገሩ አስጠነቀቃቸው። እነርሱም አምነው ልጁ ይወስደው የነበረውን ኢንሱሊን አስቆሙበት። አዎንታዊ ነገሮችን ብቻ መናገርም ጀመሩ። ማንም የስኳር በሽተኛ መድኃኒቱ ሲቋረጥበት እንደሚሆነው ሁሉ ከጥቂት ቀናት በኋላ ልጁ በመዳን ፈንታ ባሰበት፤ ደክሞም ካታቶኒክ ኮማ ወደሚሉት ወይም ፈጽሞ ወደማይነቃበት እንቅልፍ ውስጥ ገባ። በዚህ ኮማ ውስጥ ሰዎች ለወራትና ለዓመታትም ሊቆዩ ይችላሉ። ዌስሊ ግን ኮማው ውስጥ በገባ በሦስተኛው ቀን ኦገስት 22 ቀን ሞተ።

ወላጆቹ በልጁ ሞት እምነታቸው ሳይጠወልግ ሥርዓተ ቀብር በማድረግ ፈንታ የትንሳኤ ስነ ሥርዓት አስደርገውም ነበር። ልጁ ግን አልተነሣም። ይህም ከሆነ በኋላ እንኳ ለሚቀጥሉ ብዙ ወራት ከዘሚሳተፉበት የእምነት ንቅናቄ ካገኙት 'የመገለጥ እውቀት' ሊሰና በቱ አልወደዱም።

ሎሬንስ እና አሊስ ፓርከር ዌስሊ ከሞተ በኋላ በተከታዮቹ ሁለት ሳምንታት ክስ ተመስርቶባቸው ወደ ፍርድ ቀረቡ። ሴፕቴምበር 3 የዋለ ችሎትም በነፍስ ማጥፋት 15 ዓመት፥ በልጅ ማጎሳቆል ደግሞ 10 ዓመት፥ በጠቅላላ በሁለቱም ወላጆች ላይ የ25 ዓመት እስራት በየነባቸው። በዚህ ፍርድ ተይዘው ባልወጣላቸው የአንድያ ልጅ ሞት ኀዘን ላይ ጸጸት፥ በዚያ ላይ የስሕተት ልምምድ ምሬት ተሸክመው ወኅኒ ገቡ። በወኅኒ ሳሉም ጠበቃቸው ተሟግቶላቸውና ይህ ግልጽ ስሕተት ከሃይማኖታቸው ጥልቅ ትስስርና ከተሳሳተ ትምህርት የተነሣ የፈጸሙት ንጹሕ ስሕተት መሆኑን በማስረዳት ይግባኝ ጠይቆ እስራታቸው እንዲቀነስ ተደረገ። ፍርዱ ከተቀነሰ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኀዘናቸውና





ንጹሕ ስሕተታቸው ታይቶ በነፃ ተለቀቁ። እንደወጡም ይህ ስሕተት በሌሎች የዋኖች እንዳይደገም ሲሉ *We Let Our Child Die* በሚል ርዕስ ታሪኩን ጽፈው ዌስሊ ከሞተ ከሰባት ዓመታት በኋላ በ1980 አሳተሙት። ንጹሕ ስሕተት![7] እነርሱ አልፈው በተጎዱበት መንገድ ሌሎች እንዲሄዱበትና እንዲወድቁበት አልፈለጉም።

ዛሬ እንዲህ ያሉ ምስክሮችን ከአገራችን ብንጠራ ጥቂት ያልሆኑ እናገኛለን። የሞቱትን ቤት ቆጥሮት በሕይወት ያሉ መድኃኒት ጣሉ ተብለው የጣሉና የሐኪም ቀጠሮ ሰርዘው የተጎሳቆሉ፥ መነጽር የሰበሩና የተደናበሩ፥ ምርኩዝና ከዘራ ያስሰበሩና ሊራመዱ ሲሞክሩ የወደቁ፥ በሁሉም በኩል ከፈውስ ይልቅ የባሰባቸው ብዙ አሉ። ራሳቸው 'እምነት' በሚሉት ፈሊጥ ብዙ ርቀው ከሄዱ በኋላ እንደገና ወደ ሕክምና ሲመለሱ በሕክምና የመዳኑ ተስፋና ጊዜው አልፎባቸው ለሕልፈተ ሕይወት የተዳረጉ ጥቂት አይደሉም። ከዚህ አካላዊ ጉዳት ባልተናነሰ፥ ምናልባትም በባሰና በከፋ ሁኔታ የመንፈስና የእምነት ጉዳት ያገኛቸውም ጥቂት አይደሉም። በተለይ እነዚህ ደማቸውና እንባቸው ወደ ውጭ ያልፈሰሰ፥ በራሳቸው ሐሞት ራሳቸው የተቃጠሉ፥ የግርፋታቸው ሰንበርና የቁስላቸው ጠባሳ ውስጣዊ ስለሆነ ያልታየ፥ ሊደረግ የተገባው ሁሉ ያልተደረገላቸው ሰለባዎች ናቸው። እነዚህ እንደ ቤተ ሙከራ እንስሳት መሞከሪያ የሆኑ በተለይ የሐሰተኛ የፈውስ ባለ ስጦታዎች ሽንገላና ቀስት ጊጤዎች የሆኑ ናቸው። ጥቂት ያልሆኑ የፈውስ አገልጋዮች ነን ባዮች አስመሳይና አደገኛና ሰዎች ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ቁስለኞችና ጉዳተኞች ሌሎችን ከጉዳት ለመታደግ ዝም ማለት የለባቸውም። የበኩላቸውን አስጠንቃቂነት ሊያደርጉ ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የተሾሙባቸውን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ላብራቶሪ፥ ምዕመናንንም እንደ ሙከራ እንስሳት ለእንዲህ ያሉ አገልጋይ ነን ባዮች አሳልፈው መስጠት የለባቸውም። አገልጋዮችን ሲጠሩ ወይም አገልጋዮች መጥተው ለማገልገል ሲጠይቁ የአገልጋዮቹን ማንነትና ታሪክ ማወቅም፥ መጠንቀቅም፥ መጸለይም ያሻቸዋል።

ዛሬ ዛሬ ትንቢትና ፈውስ ሲባል መደነቅ በብዙዎች ዘንድ እየቀረ መጥቶአል፤ ነገሩ አግርሞት ሳይኖረው ቀርቶ ሳይሆን ውሸቱ እየበዛ በመምጣቱ ነው። ሌላው ሲያደርግ ያዩትን ምንም ሳያስቀሩ ኮርጀው የሚያደርጉ የካርቦን ኮፒ ፈውሰኞች አሁንም ብዙ ናቸው። እንዲህ ሲሆን ከተለመደና ከተደጋገመ ልምምድ የተነሣ መልካሙም ጸጋ ቀጥኖ ቀጥኖ መሳለቂያ ይሆናል፤ ተግሳጽና ማስጠንቀቂያም ኃይል ያጣሉ፤ ጉባኤም ለአደጋ ሊጋለጥ ይችላል።

---

[7] Christian Research Journal, p.1.

ልክ ቀበሮ ሳይመጣ 'ቀበሮ መጣ!' እያለ ይጮኽና መንደርተኞችን እያስበረገገ ያስወጣ እንደነበረው እረኛ ነው። አንድ ቀን እውነተኛ ቀበሮዎች መጥተው በጎቹን ሲፈጁ የወጣለት አልነበረም። እንደልማዱ እያላዘነ የነበረ ነው የመሰላቸውና ለእርዳታ አልወጡለትም። ለሰይጣን እንዲህ ያለው ዘዴም ዘዴው ነው። አረጋግቶና ትጥቅ አስፈትቶ የተለምዶ ነገር የሚሠራ አስመስሎ በጎችን ማነክ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል።

የአገራችንም ሆኑ ሌሎች የሐሰት ፈውሰኞች ከትናንት ይልቅ ዛሬ ብዙም አልተሻላቸውም። አንዳንዶች ሲሰክኑ አዳዲሶች ይፈላሉ። አንዳንዶች ስሕተታቸው ሲነገራቸው የተሻለ ማረጋገጫና አፍ የሚያስይዝ ፈውስ የሚያቀርቡ ይመስል በእልህ ይቀጥላሉ። በዚህም የጸጋ ስጦታ ዓላማና ግቦች ይዘነጋሉ። ቅንዓትና እልህ ጤናማ ጎን ቢኖራቸውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ግን የሰውን ሥራ ብቻ እንጂ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ክብር አያደርጉም። የፈውስ አገልጋይ ነን በሚሉ ሰዎች ልምምድ የተጎዱ ቢያንስ እንደነ ፓርከር ሌላውን ከመሰል ጉዳት ለመታደግ የሆኑትንና የደረሰባቸውን ነገር መናገር ይኖርባቸዋል።

የስሕተት ትምህርት ጫፉ ተቀልምሞ እንደወጋ ሹል ወይም እንደ ቀስት፥ ወይም ኪሮሽ እንደሚሉት የጌጥ መሥሪያ መርፌ ነው። መግባቱ የሚያሳምም ቢሆንም መውጣቱ ግን የባሰ የሚያሳምም ነው፤ ሥጋን ቦጭቆ ነው የሚወጣውና። የደረሰብን ብቻ አይደለንም፤ ባይደርስብንም እንኳ ኃላፊነት የሚሰማን ሁሉ የማስጠንቀቅ አደራ አለብን። አደጋ ከኖረ ትንሿም ትልቁም ማስጠንቀቂያ እንደ ዘበት መታለፍ የለባቸውም። መሪዎችም እንደ ውቂያ በሬ አፋቸው የተሸበበ ሊሆን አይገባም። የቃሉ ማስጠንቀቂያም ሆነ ከጉዳት የሚገኙ ገጠመኞች የሚሉት ነገር መሰማትና መደመጥ መስተዋልም አለበት። አንዳንዶች በቀላሉ እመረቡ ውስጥ የሚገቡ እነርሱን የሚስባቸውም፥ እነዚያም የሚያቀርቡላቸው ነገር መኖሩ ነው። እነዚህ ሰዎች ገብተው በዚያው ተይዘውና ተጠላልፈው የሚቀሩበት ሁኔታም አለ። በሰሜን አፍሪቃ በአልጄሪያና በሞሮኮ የሚኖሩ ገበሬዎች ዝንጀሮዎችን በቀላሉ የሚይዙበት ዘዴ አላቸው። ጠንካራና ትልቅ ቅል ወስደው የዝንጀሮ እጅ ብቻ ሊያስገባ የሚችል ትንሽ ክብ ቀዳዳ ቀርፈው ካወጡለት በኋላ በውስጡ የተቆላ ለውዝ አድርገውበት በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ በጥብቅ አስረው ያስቀምጡታል። ዝንጀሮ ቀንም ይሁን ወይም ማታ ለአዳኑ ወደ ዛፉ ሲመጣ የለውዙ ሽታ ይስበዋል። በደመ ነፍስም ስግብግብ እጁን በቀዳዳው ይሰድድና በእጁ ሙሉ ይዘግናል። ቀዳዳው ግን ያልተጨበጠ እጅ ለማስገባት እንጂ የተጨበጠ እጅ ለማስወጣት የማይችል ጠባብ ነው። ዝንጀሮም እጁን ለማስወጣት የጨበጠውን መልቀቅ እንዳለበት የሚረዳ አስተዋይ አይደለምና ድንጋጤውም ተጨምሮበት ሲታገል አጥማጆቹ መጥተው ያለምንም ትግል





ምርኮኞቻቸውን ይዘው ይሄዳሉ። አንዳንድ አሳቾችም ይህን የመሰለ ማታለያ መረብ ዘርግተው ሽታ ባለው ነገር ይስባሉ፤ የሚሰጡት ነገር ግን የለም። እንዲያውም በተቃራኒው እያዘገመ የሚመጣ ጉስቁልና ነው ያለበት። ክርስቲያን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማስተዋል ዐይኖቹን መክፈት አለበት።

ሌላው መስተዋል ያለበት ነገር ክርስትና ከጸጋ ስጦዎች፥ ያውም ከጥቂት የጸጋ ስጦታዎችና ከአገልግሎትም ያለፈ ነገር መሆኑ ነው። ክርስትና የባህርይና የኑሮ ጉዳይ ነው። ክርስቶስን ለመምሰል የሚደረግ መለወጥና ትግል ነው። ከዚህ በቀደመው መጽሐፍ በሁለተኛው ምዕራፍ ውስጥ ስለ ጸጋ ስጦታዎች በዝርዝር እንደተጻፈው የጸጋ ስጦታዎች እግዚአብሔር ለአካሉ፥ ማለት፥ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽና አገልግሎት በጸጋው የሰጣቸው ስጦታዎች ናቸው። እያንዳንዱ በአካሉ ውስጥ ያለ ክርስቲያን የአካሉ ብልት ነውና ቢያንስ አንድ ስጦታ አለው። ስጦታ የሌለው ክርስቲያን የለም። በአንጻሩም አንድ ሰው የሁሉም ስጦታዎች ጎተራም አይደለም። ይህን እውነት ማወቅ በክርስትና ሕይወታችን ላይ የሚፈጥረው ለውጥ ታላቅ ነው። አንድ ሰው የጸጋ ስጦታውን ለይቶ ማወቁ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖር፥ ወጥቶ የሚገባ ያልታወቀ ሰው ብቻ እንዳይሆን ያደርገዋል፤ በአካሉ ውስጥ ያለውን ፍሬያማነትና ተሳትፎም እጅግ ከፍ ያደርገዋል።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደ ጸጋ ስጦታ የተነገሩት ስጦታዎች ሁሉ ዛሬም አሉ፤ ይሠራሉም። ፍጹም የሆነው እስኪመጣ ድረስ የቱም የጸጋ ስጦታ አይሰረዝም። አገልግሎቱም አያበቃም። በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን ምሑራን ጥናት ይህ ፍጹም የሆነው ነገር የአዲስ ኪዳን ቀኖና መጠናቀቅ ነው። ከእነዚህም መካከል አወዛጋቢ የሆኑቱ ስጦታዎች ከአዲስ ኪዳን ቀኖና መጠና ቀቅ ጋር ተቋርጠዋል የሚሉ *Cessationists* የሚባሉ አሉ። በአንጻሩ ደግሞ ገሚሱ ሊቃውንት ስጦታዎች ሁሉ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ድረስ ይቀጥላሉ፥ ፍጹም የሆነው የተባለውም የጌታ ዳግም መምጣት ነው ይላሉ። የኔም መረዳት ይህኛው ነው። ይህ ፍጽምና የክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። ምንም እንኳ በጣም አብረቅራቂ ተደርገው በሰዎች የሚታዩ ሁለት ወይም ሦስት ስጦታዎች፥ በተለይም በልሳኖች መናገር፥ ከበረከታቸው ጎን ችግርና መለያየት እስኪፈጥሩ ድረስ ቢጋነኑም እነዚያንም ጨምሮ ስጦታዎች ሁሉ ዛሬም አሉ፤ ይሠራሉም። የልሳኖች ቀውስ በአንድ በኩል በልሳኖች ከመናገር አትከልክሉ የሚለውን የሚተላለፉት ሊከለክሉ ሲሞክሩ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በልሳን የሚናገር ቢኖር እንዲተረጉም ይጸልይ፥ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር የሚለውን የሚተላለፉት ደግሞ ከመስመር ሲወልፉ የሚፈጠረው ችግር ነው። መገለጥ የሚባለውን ነገር እንዲሁም ትንቢትንና ፈውሶችን ተከትለው

የሚመጡ ውዥንብሮችም ጥቂት አይደሉም። ልምምድን ከቃሉ ትምህርት በላይ በሚያደርጉ ሁሉ ዘንድ በቀላሉ መወናበድና ወደ አዳዲስ የስሕተቶች ማጥ ውስጥ መግባት አለ። በአንጻሩ ደግሞ የጸጋ ስጦታዎች እንደሌሉ መቁጠር በሕይወት፥ በአምልኮና በአካል ውስጥ ቅዝቃዜን የሚፈጥር ችግር ያስከትላል። በቃሉ መሠረትና በታቀደላቸው ዓላማ ስጦታዎች ቢተገበሩ ምዕመናን ይታነጻሉ፤ ይህ ዋና ዓላማቸው ነውና። ቦታቸውን ከለቀቁና እንደ ቃሉ ካልተደረጉ ግን ችግር መፈጠር ብቻ ሳይሆን እንዴት የተሳሳቱ ልምምዶችና ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ በዚህም በቀደመውም መጻሕፍት ውስጥ ተዘክሮአል። እንግዲህ የጸጋ ስጦታዎች አሉ። ለቤተ ክርስቲያን መታነጽም አስፈላጊ ተደርገው ከጌታ የተቸሩን ናቸው።

ነገር ግን ከስጦታዎች ባሻገር እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ሌላ ነገር መኖሩን እንድናስተውል ያሻል። ያም የጸጋ ስጦታዎች በውስጣችን ሊሠሩት የማይችሉት፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ብቻ በሕይወታችን ውስጥ ሊሠራው የሚችለው መንፈሳዊ ባህርይ ነው። ይህም ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት ነው። በእግዚአብሔር ዕቅድ እኛ የጌታን ፈለግ እንድንከተል፥ የልጁን መልክ እንድንመስል አስቀድሞ ወስኖአል፤ ሮሜ. 8፥28-30፤ 1ቆሮ. 11፥1፤ ኤፌ. 5፥1-2፤ 1ተሰ. 1፥6፤ ወዘተ። ሰይጣን የጸጋ ስጦታዎችን ሁሉ አስመስሉ ሊሠራቸው ይችላል። ባህርይን ግን ከቶ ሊሠራ አይችልም። በዚህች በወደቀች ዓለም የመንፈስ ፍሬ ሁሌም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚመስሉ ባህርያት ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎችም የምናገኝበት ጊዜያት አሉ። ክርስቲያን ሳይሆኑ ታጋሾች ወይም የዋሆች የሆኑ ሰዎች ይኖራሉ። ይህ የሰውም መጠናዊ ግብረ ገባዊ ፍጡርነት የሚያሳይ ነው። በዳኑት ዘንድ ግን እነዚህ ነገሮች እንደ ባህርይ፥ እንደ ኑሮ፥ እንደ ሕይወት ዘይቤ የሚጠበቁ ናቸው።

ከስጦታ ባሻገር ልንጋደልለት የሚገባ ሌላው ነገር የመንፈስ ፍሬ ነው። ክርስቲያን ክርስቲያን ከሆነ በኋላ መንፈሳዊ ወይም ሥጋዊ ክርስቲያን ሆኖ ሊኖር ይችላል። ሥጋዊነቱ የጸጋ ስጦታ ወይም አገልግሎት እንዳይኖረው ላያደርገው ይችላል። የመንፈሳዊነት ምልክት የጸጋ ስጦታ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ ነው። ሰይጣን የጸጋ ስጦታዎችን አስመስሎ መሥራት ይችላል። ራሱ የብርሃን መልአክ፥ አገልጋዮቹም የጽድቅ አገልጋዮች ሊመስሉ ራሳቸውን መለወጥ ይችላሉ። የመንፈስ ፍሬን ግን መፍጠር ከቶም አይችልም። የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው፤ ገላ. 5፥22-23። ይህንን ፍሬ በጸጋ ስጦታናበአገልግሎት ውስጥ አናይም። ይህ ፍሬ የሚታየው በባህርይ ውስጥ ነው። በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በጸጋ ስጦታዎች ዝርዝርና የቆሮንቶስ ምዕመናን እንቁልልጭ





በሚጫወቱባቸው በሁለቱ ስጦታዎች መካከል የፍቅርን ነገር መጻፉ አገልግሎቶች ሁሉ ያለ ፍቅር ከንቱ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ፍቅር የሚገለጠው በባህርይ ውስጥ ነው።

ክርስትና በእምነት ጸንቶ መኖርም ነው። ምንም ይሁን ምንም ይምጣ በቤቱ ከእርሱ ጋር ተጣብቆ መኖር ነው። እምነትን የዘመናዊው መነቃቃትና ተሐድሶ እንዲሁም የካሪዝማዊ ንቅናቄ አራማጆች፥ በተለይም የቃል-እምነት ሰባኪዎች እንደማትጨበጥ አሟላጭና ረቂቅ ነገር አድርገው ቢተረጉሙትም እምነት እንደውኃ ውስጥ ዓሣ የማይጨበጥ ዓይነት ምስጢርና የማይዘግኑት ጉም አይደለም። በዕብ. 11 በሰፊው እንደምናገኘው እምነት የተስፋ ማረጋገጫና የማናየው ነገር አስረጅ ነው። በምዕራፉ ውስጥ የተዘረዘሩትና ከዝርዝሩ ውጪ እንዳሉ የተጠቀሱት ሰዎች በዚህ መታመን እግዚአብሔርን ያስደሰቱ ሰዎች ነበሩ። በምዕራፉ የተጠቀሱትና ታሪካቸው በብሉይ ኪዳን ተዘክሮ የምናገኛቸው እነዚህ ሁሉ ሰዎች ሁሌም በአሸናፊነት ከተራራ ወደ ተራራ እየዘለሉና በደመናት ላይ እየተንሳፈፉ የኖሩ አልነበሩም። በተለይ የመጨረሻውን የምዕራፉን ክፍል ስናጠና ሦስት ዓይነት ሰዎችን እናገኛለን። አንደኛው ወገን በእምነት የወረሩ ወራሪዎች ወይም ወራሪ እምነት ያላቸው ናቸው። እነዚህ መንግሥታትን ድል የነሡ፥ የአናብስትን አፍ የቆለፉ፥ የእሳትን ኃይል ያጠፉ እንዲህ የመሰሉት ናቸው። ይህን ያደረጉት በእምነት ነው። ሁለተኞቹ ሲሸሹ፥ ሲያፈገፍጉ፥ መከራ ሲቀበሉ የሚታዩ ባለ መከራ ተቀባይ እምነት ሰዎች ናቸው። እኒህ ደግሞ ሲገረፉና ሲደበደቡ፥ መዘበቻ ሲሆኑ፥ በወኅኒ ሲፈተኑ፥ ሁሉን እያጡና መከራን እየተቀበሉ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ሲዞሩ፥ በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ሲቅበዘበዙ የሚታዩ ናቸው። ይህን ያደረጉትና የተቀበሉትም በእምነት ነው። ሦስተኞቹ ደግሞ ሞትን ሲቀበሉ የሚታዩት ናቸው። እኒህ ደግሞ በድንጋይ ተወግረው፥ በመጋዝ ተሰንጥቀው፥ በሰይፍ ተገድለው የሞቱት ናቸው። እኒህም የሞቱት በእምነት ነው። የወረሩትም፥ ያፈገፈጉትም፥ የሞቱትም በእምነት ነበር። እምነት እንግዲህ የምንፈልገውን ነገር ፈጥረን ካለመኖር ወደመኖር የምናመጣበት ምትሃት ሳይሆን እርሱ በመነጠረልን ጎዳና የምንሄድበት በተስፋ ሰጪው ታምነን የምንኖረው ኑሮ ነው።

# መቋቋም

የስሕተት ትምህርቶችንና ልምምዶችን ስለማስተዋል ይህን ያህል ከተባለ ከድምዳሜ በፊት ስለመቋቋምና ስለመቋቋሚያ ስልቶችም ጥቂት መባል አለበት። የስሕተት ትምህርትና ልምምዶችን ለማወቅ ገልጦ መናገር፥ መጋፈጥ ካልቻሉ መራቅ፥ መሸሽ አንድ ጥበብ

ነው። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የስሕተት ትምህርቶች በከፊል በውኃ ውስጥ ከተደበቀ ዐዞ ጋር ተመሳስሎአል። አስተውሎ ከመነከስ መራቅ ድንቅ ነገር ነው፤ ከተነከሱም በዐዞ ተጎድቶ እንደተረፈው አሳርም እንደተባለው ሰው ከሰውነት አንዱን ብልት አስወስዶም እንኳ በቀረው መኖርም ጨርሶ ከመበላት የተሻለ ነው። አሳርም ፊሪ የተባለው ይህ ሰው በደቡብ አፍሪቃ ናታል በሚባለው ግዛት ውስጥ በሚገኘው 'የዓዞ ወንዝ' እየተባለ በሚጠራው ወንዝ ሳለ በድንገት በአንድ ዓዞ እግሩ ተነከሰ። ሰውየው በእጁ የሞት ሽረት ትግል ታግሎ እግሩን ሲያስለቅቅ ዐዞው እግሩ ሲያመልጠው ታግሎ ቀኝ እጁን ነከሰውና አልለቅ አለው። ፊሪም እየጮኸና እየታገለ በግራ እጁ ሰንጢውን መዝዞ ዓዞውን ወጋው። እንዲያም ሆኖ አልለቀቀውም። በመጨረሻም ዓዞውን ሊያሸንፍ ያለመቻሉን ያየው ፊሪ ካላሸነፈው ደግሞ ነፍሱንም ሊያጣ እንደሚችል ተረድቶ በሰንጢው የተጎዳውን ቀኝ እጁን ከመጋጠሚያው ቆረጠና ደሙን እያዘራ ሸሸ። የስሕተት ትምህርቶችን መረማመጃ መስሎአቸው የረገጡና የተነከሱ የብዙ ብዙ ናቸው። በትንቢተኞች ከሥራቸው የተፈናቀሉ፥ ንብረታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል በትንቢተኞቹ የተወረሱ፥ ከአገልግሎት የራቁ፥ በበሽታ የተጠቁና የሞቱ፥ በኃጢአት የወደቁ፥ ውሸታም የተስፋ ጉም ሲዘግኑ እጃቸው አልሞላ ብሎ የተወናበዱ፥ የቅዠትና የሕልም ዓለም ውስጥ የገቡ፥ መንፈሳዊ መታለል፥ የሞራል ውድቀት፥ ትዳራቸው ፈርሶ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ስብራት የደረሰባቸው ጥቂቶች አይደሉም። ስለዚህ ነው አስጠንቃቂነትና ጠንክሮ መቋቋም ማስፈለጉ።

# የመቋቋሚያ ስልቶች

የስሕተት ትምህርቶችንና ልምምዶችን ለመቋቋም ዓይነተኛ ና ቸው የምላቸው አራት ዋና ዋና ነጥቦች እኒህ ናቸው።

አንደኛ፥ የስሕተት ትምህርቶችንና የተሳሳቱ ልምምዶችን ምንነት ለይቶ ማወቅ እና ማሳወቅ። አንዳንድ ትምህርቶችና ልምምዶች በጣም ጤናማ ይምሰሉ እንጂ ወጥመዶች ናቸው። አንቀው ይዘው እዚያው የሚያስቀሩ፤ ከመንፈሳዊ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ከእውነትም የሚያስቀሩ ናቸው። መልካቸውና ቅርጻቸው ብቻ ነው መንፈሳዊ የሚመስለው እንጂ ከቃሉ ትምህርት ያፈነገጡ ናቸው። ስለዚህ በሽፋን አንታለል። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ነፍሳት የሚበሉ አትክልት ናቸው። አትክልት የሚበሉ ነፍሳት ሳይሆን ነፍሳት የሚበሉ አትክልት። አትክልት ውኃ ከመሬት እየመጠጡና ፀሐይ ብርሃን ምግባቸውን እየሠሩ የሚያድጉ ብቻ ይመስለናል። በእርግጥ ይህ የአትክልት ሁሉ ባህርይ ነው። ነገር ግን ካደጉ በኋላ በተለይ ሥጋ የሚበሉ አትክልት መኖራቸውን ብዙዎቻችን





አናውቅም። ከነዚህ ተክሎች እስከዛሬ ካሚታወቁት ዋናዎቹ በአጠቃላይ አምስት ዓይነት ናቸው። የሚበሉትን ሥጋ የሚይዙባቸውም ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው። ይህ የተክል ሳይንስ ጥናት ቢመስልም የታወቁትን ሦስቱን በጣም በትንሹ እንያቸው። ሦስቱን የመረጥሁት የማጥመጃ መንገዶቻቸው የተለያዩና በምሳሌነት አስጠንቃቂ የሆነ ትምህርት ሰጪ ስለሆኑም ነው።[8]

የመጀመሪያዎቹ ነፍሳት የሚያጠምዱበት በላዩ ክዳን ያለበት ኩባያ የሚመስል ቅጠል አላቸው። ለምሳሌ ሳራሴኒያ የሚባሉት ተክሎች ነፍሳቱን ለመሳብ የሚያመቻቸው በኩባያ መሳይ ቅጠሎቻቸው ጫፍ ላይ ደማቅ ቀለም፥ ጣፋጭ ጣዕምና አስካሪ የሆነ ሽታ አላቸው። ይህ ዋና የመሳቢያ መሳሪያቸው ነው። በኩባያ መሰሉ ውስጠኛ ክፍል ደግሞ በጣም ለስላሳና የሚያድጥ ፈሳሽ አለበት። ወደ ውስጥ የሚገቡትን ነፍሳት የሚፈጨው ይህ ፈሳሽ ነው። ሌሎቹ ድሮሴራ የሚባሉት ተክሎች ደግሞ በአበባቸው ውስጥ ቀጫጭን ሙጫ የሚያመነጭ ግድግዳና ጸጉሮች አሏቸው። ሙጫዎቹ የሚመነጩት አንድ ነገር ሲያርፍባቸው ነው። ለምሳሌ አንዲት ዝንብ መጥታ ካረፈችበት የስኳርነት ጣዕም ያለው ሙጫ ይመነጭና ዝንቧን አጣብቆ እዚያው ያስቀራታል። ወዲያውም ጸጉር መሰል ነገሮቹ መንቀሳቀስና እንደ መረብ ሆነው ማጥመድና ማሰር ይጀምራሉ። ከዚያ ምግብ ናት። ሌሎቹ ደግሞ ከትልልቅ ነፍሳት እስከ ትንንሽ እንቁራሪቶች ድረስ ያለችግር መብላት የሚችሉት ዲዮኒያ የሚባሉት ተክሎች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ የቬኑስ የዝንብ ወጥመድ የምትባለው ቆንጆ አበባ ያላት ተክል ትገኛለች። የቬኑስ ወጥመድ አበባ መልኳ ቀይ ሆኖ መከፈትና መዘጋት በሚችሉ የጎድን አጥንት ቅርጽ ባላቸው መሸፈኛዎች የተሠራች አበባ ናት። መከፈትና መዘጋት የሚችልበት መካከለኛ ቦታ ልክ እንደ መዝጊያ ማጠፊያ የመሰለ ነገር ነው። አበባዋ በምትከፈትበት ጊዜ ቀይ አበባ፥ ስትዘጋ ደግሞ ሙዝ ወይም የባቄላ እሸት ይመስላል። ተከፍታ ሳለ ምንም ነገር በላይዋ ሲያርፍ ወዲያው ትዘጋለች፤ ከዚያም የተያዘው ሰለባ ምግብ እንዲሆን የሚፈጫቸውን ፈሳሾች መመንጨት ይጀምራሉ። ሥጋ በሊታ ተክሎች የሚበሏቸውን ነፍሳት አገር ላገር እየዞሩ አያድኑም፤ በአንድ ቦታ የተተከሉ ተክሎች ና ቸውና። ግን ረቂቅ የሆነ መሳቢያ ተፈጥሮ አላቸው። ያ ምግባቸውን ይስብላቸዋል።

የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶችም ልክ እንዲህ ይመስላሉ። መልካቸው ያማረ ግን የማይበሉት የሚመስሉትን የሚበሉ፥ የሚሰለቅጡ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች የሚመስሉ ናቸው። መልካቸውን ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ምንነታቸውን ቢያውቁ ኖሮ ሰለባ የሚሆኑት ነፍሳት ባልቀረቡአቸው ነበር። ስለማያውቁ ግን

---

8 ምንጭ፥ *Compton's Interactive Encyclopedia*. Copyright © 1997 TLC, Inc. የተለያዩ ቦታዎች።

ሊቀስሙ ገብተው ስንቅ ሆነው ይቀሩላቸዋል። ማወቅ ትልቅ ጥቅም፥ አለማወቅም ትልቅ ጉዳት ነው። ተራው ሰው ነፍሳት የሚበሉ አትክልት መኖራቸውን እንደማያውቅ ሁሉ ከተርታው ምዕመን ብዙውም በቀላሉ አማኝና ጀሌ ነው። ከዚህ ግን ማለፍ አለበት።

ሁለተኛ፥ ሚዛናዊነት። ስሕተቶች ሁሌም ወደ ሁለት አፈንጋጭ አክራሪ ዋልታዎች ይሄዳሉ። ሰዎች ተሳስተው ወደ አንዱ ጫፍ ሲሄዱ እነሱን ለማስተካከል በማለት ወደ ሌላኛው ጫፍ ሄዶ መቆም ተገቢ አይደለም። 4+2 9ነው ካሉን እነርሱን ወደ ትክክለኛው መልስ ወደ 6 ለማምጣት ብለን፥ 'የለም 3 ነው' ብንል ራሳችንን ስሕተተኛ ነው የምናደርገው። ሁሌም ጤናማውንና ትክክለኛውን መያዙ ተገቢ ነው። አራት ሲደመር ሁለት 9ም 3ም አይደለም። አንዱ፥ 'ሰው አምላክ ነው' ካለ እርሱን ለማረም፥ 'የለም፥ አይደለም። ዳዊት ሰው ትል ነው፤ ቁንጫ ነው ብሉአልና እንዲሁ ነው' ብለን መድረቅ የለብንም። ሰው ሰው ነው፤ አምላክም አይደለም፤ ትልም አይደለም። ወይም አንዱ፥ 'ልሳን መናገርህ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ የመኖሩ ምልክት ነው ያለዚያ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ የለም' ካለ፥ 'የለም፥ እንዲያውም ልሳን ከአጋንንት ነው' ልንል አይገባም። በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ ውስጥ የልሳኖች ቀውስ በሚለው ንዑስ ርእስ ስር ሰዎች ከሰይጣንም ከራሳቸውም ይህንን ስጦታ ሊለማመመዱ የሚችሉበት ሁኔታ ተጽፎአል። የብዙዎችን የልሳን ተናጋሪዎች ልምምድ ስናጤን የሥጋ ፈጠራና ተለማምደው የሚሉት መሆኑ በጣም ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ እዚህም ላይ ጤናማ ሚዛንን መጠበቅ አለብን።

በዘመናዊዎቹ የተሐድሶና መነቃቃት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የምናያቸውን ልምምዳዊነትና ፈር የሳተ አፈታት መጥቀሳችን ራሳችንን እንዳናይ ማድረግ የለበትም። ረዥም ጊዜ መጸለይን ማጥላላት ለራሳችን የጸሎት ሕይወት ድካም መሸፈኛ መሆን የለበትም። የታወከ አምልኮ እንደሆነ የሚመስለን አምልኮ ከልብ የመነጨ ያልተከለከለ መስዋዕታችንን እንዳንሰዋ እንቅፋት መሆን የለበትም። እግዚአብሔር ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጸሎትን ለሌላዋ ቃልን፤ ለአንድዋ መመስከርን ለሌላዋ ገንዘብን፤ ለአንድዋ አምልኮን ለሌላዋ ሥራን ወዘተ ለያይቶ አልሰጠም። ምንም እንኳ የተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች ከእነዚህ ወይም ከሌሎቹ ወደ አንዱ ቢያቀርቡንም ቤተ ክርስቲያን ሚዛናዊ መሆን አለባት። እምነት አለኝ ብላ ሥራን መርሳት የለባትም። የኛ ኃላፊነት ጸሎት ነው ብላ መመስከርን መዘንጋት የለባትም። ሚዛናዊ ክርስትና ያሻናል።

ሦስተኛ፥ ቅንነት ባለበት ድፍረት ስሕተትን ገልጦ መናገር። እርግጥ ስለማናውቀው ነገር መውቀስ፥ መገሰጽ፥ ማረም





አይቻለንም። ነገር ግን አትውቀሱ፥ አትፍረዱ የሚለውን መሸፈኛ አልፎ ግልጽና ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ነገር ከኖረ ያወቁትንና የተረዱትን ስሕተት መናገር ትክክለኛ እርምጃ ነው። ነጭና ጥቁር ሆኖ በግልጽ የሚታይ የተሳሳተ ትምህርት፥ ከቃሉ ጋር የሚጣላ ልምምድ ሲሰበክ የሰውን ልብና ግፊት መመርመር አንችልም ፈራጅ እሰኛለሁ ብለን ዝምታ በራሱ ስሕተት ነው።

አራተኛና የመጨረሻው ወደ ሥልጣኑ ምንጭ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መመለስ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ጊዜ ያለፈበት የሚመስል፥ ግን ጊዜ የማይሽረውና ጊዜን ራሱን የሚያሳልፍ ቃል ነው። ሞኝነት ይመስላል፥ ግን የጥበብ ምንጭ ነው። አሮጌ ነው፤ ግን ዛሬ ከማተሚያ ቤት የወጡት ትኩስ መጽሐፎች ከእርሱ ጋር ሲወዳደሩ ቀድሞውኑ አሮጌ ሆነዋል። ኋላ ቀር ይመስላል ግን ገና ከሚመጣውም ቀድሞ የሄደና ያላየነውን የሚናገር፥ ያልደረስንበትን ያየ እውነተኛ መሪ መጽሐፍ ነው። ለአንዳንዶች የቆረፈደ ምግብ ይመስላል ግን ገንቢና ትኩስ የሆነ የነፍስ አልሚ ምግብ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ከምንም ዓይነት ልምምድ በላይ ነው። ስለዚህ ነው ጴጥሮስ በተራራ ላይ ያየውንም አስገራሚ ልምምድ ከዘከረ በኋላ ቃሉ ከዚያም የበለጠ መሆኑን ሲገልጥ፥ 'ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን' ያለው፤ 2ጴጥ1፥19።

አንድ ክረምት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለዘመቻ ጋምቤላ ሄደን ነበር። አገሩ ከሰው ቁመት በላይ በሆነ ሳርና በዛፎች የተሸፈነ ሜዳማ አገር ነውና በሚሄዱበት መንገድ ምልክት ማድረግ አስቸጋሪ ነው። አንድ ቀን ወደምንሠራበት ጣቢያ ስሄድ የተሳሳተ መንገድ ወሰድኩና ጠፋሁ። ለኔ የመሰለኝ በትክክለኛው መንገድ ያለሁ ነው፤ ግን ተገንጥሎ የወጣ የተመነጠረ መንገድ ይዤ ነበር የምሄደው። ብዙ ሄጄም የምንሠራበት ስፍራ አልደረስኩም፤ ቀጥዬ ብሄድም ጸጥ ረጭ ያለ ደን ውስጥ ነው ያለሁት። ወደ ሩብ ሰዓት ያህል ሄጃለሁና ቦታው ያን ያህል እንደማይርቅ አውቄ የተሳሳተ መንገድ ላይ መሆኔን ተረዳሁ። ወዲያው ያደረግኩት በዚያው መንገድ ወደኋላ መመለስና እስከተሳሳትኩበት የመገንጠያ መንገድ ድረስ መምጣት ነበር። መጥቼ መገናኛው ቦታ ከደረስኩ በኋላ መሄድ የነበረብኝን ትክክለኛውን መንገድ አገኘሁት። በዚያ መንገድ ላይ ሌሎችም ተማሪዎች ሲሄዱበት አገኘኋቸውና አብሬአቸው ሄጄ እስፍራዬ ደረስኩ። መንገዴን ለማግኘት እስከተሳሳትኩበት ነጥብ ድረስ መምጣት ነበረብኝ። የሐሰተኛ ትምህርቶች ዋና ስሕተት ከቃሉ ማፈንገጥ ወይም ቃሉን እንዳይሆን አድርጎ መተርጎም ነው። ለመታረም ማድረግ ያለባቸውም የሚያደርጉትንና የሚያስተምሩትን ነገር በግልጥ ወደሚዳኝ ወደ እውነተኛው የሥልጣን ምንጭ ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ ነው። ቀደም ሲል የተጠቀሰው ጂም ቤከር መሳሳቱን ያወቀው ቃሉን እንደቃሉ አድርጎ ሲመረምር ነበር።

በተሳሳቱ ትምህርቶችና ልምምዶች ውስጥ ያሉ ሰዎችም ማድረግ ያለባቸው ነገሮች አሉ።

1፥ ቀደም ሲል እንደተባለው ከእንዲህ ያሉ ትምህርቶችና ልምምዶች ጋር መጋፈጥ ካልተቻለ መሸሽ አንድ እርምጃ ነው።

2፥ መላቀቅና መጣበቅ፤ ከተሳሳተው መላቀቅና ከእውነተኛው መጣበቅ። ባሉበት ስፍራ የሚሰጠው ትምህርት ከቃሉ ያፈነገጠ መስሉ ከታያቸውና ያንን ማረም የማይቻላቸው ከሆነ እዚያ መቀጠል የለባቸውም። ቃሉ የሚሰበከበትንና እንደቃሉ ለመኖር ጥረት የሚደረግበትን ቤተ ክርስቲያን ፈልጎ በዚያ መሆንና ራስንና ሌላውን ማነጽ አለባቸው እንጂ በመፈራረስ ውስጥ መኖር የለባቸውም።

3፥ እምነት ተናግቶ በሐሰተኛ ልምምድና ትምህርት ተለውጦ ከሆነ ይህን በጥብቅ መመርመር ያስፈልጋል። ጌታን በምታከብርና ቃሉን በምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገኝተው ከአገልጋዮች ጋር ሲማሩና ሲለማመዱ የኖሩት ነገር ምን መሆኑን በግልጽ በመንገር ያ ትምህርትና ልምምድ ትክክለኛ መሆንና አለመሆኑን ለመረዳት መፍቀድ አለባቸው። ትክክለኛ ያልሆኑበትንና ከቃሉ የተረዱትን ዝተት ያለቅሬታ መጣል አለባቸው።

4፥ በግል የእግዚአብሔርን ቃል በትጋትና በሥርዓት ማጥናት። አንድ ክርስቲያን ተግቶ ቃሉን የሚመረምር ከሆነ እውነተኛውን ያውቃልና በሐሰተኛ ትምህርት ተወናብዶ በቀላሉ አይወሰድም። በዚህ ዘመን ብዙ የተጭበረበሩ ገንዘቦች እየተመረቱ ይወጣሉ። እሠራ በነበረበት አንድ መሥሪያ ቤት እንዲህ ያሉ የገንዘብ ኖቶች የሚመረመሩበት የተለየ ሰማያዊ መብራት ያለው ትንሽ መሣሪያ አለ፤ ኖቱን በመብራቱ ሥር ስናደርገው ሐሰተኛው ብር የተለየ መልክ ይኖረዋልና አንቀበልም። የሐሰት ብር አምራቾች በየጊዜው የሚሠሩትን ቴክኖሎጂዎች የሚያልፍ ብር መሥራት ይችላሉና አዳዲስ ዘዴዎችን ሁሉ ጨርሶ ማስተማር የማይቻል ነው። የአሜሪካ ባንኮች ይህን ችግር ለማቃለል የደረሱበትና ሁነኛ ሆኖ ያገኙት አንድ ዘዴ ነው። እነዚህ ባንኮች የገንዘብ ኖት የሚቀበሉና የሚሰጡ ሰዎቻቸውን ሐሰተኛውን ገንዘብ ከእውነተኛው በቀላሉ እንዲያውቁ የሚያደርጉበትን ስልጠና ለሁለት ሳምንት ይሰጡአቸዋል። በመጀመሪያው ሳምንት አምስቱንም የሥራ ቀናት እውነተኛውን ገንዘብ ያስቆጥሩአቸዋል። ሠልጣኞቹ በሚቀጥለው ሳምንት የተጭበረበሩ የገንዘብ ዓይነቶችን እናያለን ብለው ሲጠብቁ በሁለተኛው ሳምንትም አሁንም አምስቱንም ቀን እውነተኛውን ገንዘብ ሲያስቆጥሩ ያሰነብቱአቸዋል። ከሁለት ሳምንት በኋላ በቃ ጨርሳችኋል ብለው ወደ ሥራ ያሰማሩአቸዋል። ዓላማቸው እውነተኛውን ካወቁ ሐሰተኛውን በቀላሉ ያውቁታል የሚል ነው። እውነትም፥ በሦስተኛው ሳምንት እነዚህን ሰዎች ለመፈተን የተጭበረበረ ገንዘብ በእውነተኛው ውስጥ ደባልቀው እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ። ሰዎቹም ገና የጣታቸው ጫፍ





የተጭበረበረውን ገንዘብ እንደነካው ምዝዝ አድርገው ያወጡታል። እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል መብላት ሐሰተኛው ሲመጣ ገና በሩቅና በሽታ ለመለየት ያስችላል።

*ሕግህን ለሚወዱ ብዙ ሰላም ነው፤ ዕንቅፋትም የለባቸውም።* መዝ. 119፥165

*የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማልና።* 2ጢሞ. 3፥16

# ሀሙዳየ ቃላት

**ሁኔታዊ ስነ ምግባር** (situational ethics) *በነዋሪው ሕግ ሳይሆን ሁኔታዎችን ተመርኩዞ በሚወሰን ውሳኔና ውጤት ላይ የሚደገፍ ፍልስፍና ወይም ስነ ምግባር። እንዲህ የመሰለው ስነ ምግባር ወይም ፍልስፍና ከነገሮችና ሁኔታዎች ምንጭ ይልቅ በውጤታቸው ላይ የሚያተኩር ነው። ስለዚህ ውጤቱ ጥሩና ተፈላጊ ከሆነ በምንም መንገድ ቢገኝ ክፍፋት የለበትም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነው።*

**ሃስዮተ ጽሑፋት እና ሃስዮተ ልሳናት** (textual criticism and linguistic criticism) *የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ስነ ጽሁፋዊና ልሳናዊ ወይም ቋንቋዊ ትክክለኛነት የተፈተሸበት የጥናት መስክ። ሐስዮተ ጽሑፋት እና ሐስዮተ ልሳናት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና በስብከትና ማስተማር አገልግሎት ተገቢ ሚናቸውን ማጣት የለባቸውም። በተለይ በትርጉም ሂደት ውስጥ እነዚህ የዋና ጽሑፎችና የተተረጎመው ትርጉም ውጪያዊና ውስጣዊ ተመሳሳይነትን እንዲሁም የዋናውን ቋንቋና የተቀባዩን ወይም የተተርጓሚውን ቋንቋ የቃላት ምጠና የሚያጠናና የሚመለከት ሥራ ነው። በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ያለው ታሪካዊና ባህላዊ ርቀትም አብሮ ይታያል።*

**ልምምድ፥** *ልምምዳዊነት ልምምዳዊነት የካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ጉልህ ባህርይ ነው። ከአንድ ጥቅስ ወይም ክፍል በመንደርደር ያ ነገር እንዲሆን ወይም እንዲፈጸም ከመሻት የተነሣ 'የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?' ሳይሆን፥ 'በውጤቱ ያ የተፈለገው ነገር ሆነ ወይስ አልሆነም? ምን ተፈጸመ?' በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ማተኮር ነው። ምንም ሆኖ በውጤቱ የሚፈለገው ነገር ከተፈጸመ ግብ ተቆጠረ ማለት ነው። በዚህ ነገር ውስጥ የተዘነጋ ነገር አለ፤ ያም፥ የተገኘው ነገር ወይም ውጤት የተገኘበትን መንገድ ሁሌም ትክክለኛ ሊያደርገው ያለመቻሉ ነው። ይህ ሰዎች በልሳን እንዲናገሩ በሚደረጉ ግፊቶች ውስጥ በሰፊ የሚታይ ልምምድ ነው።*

**ሐሰተኛ ነቢይና ሐሰተኛ አስተማሪ** *በእግዚአብሔር ስም ይህን ይላል እግዚአብሔር እያለ ሐሰትን የሚናገር አሳች፤ ከቃሉ እውነት ጋር የሚጋጭ ትምህርትን የሚያስተምር ሰው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ሰዎች እንዲህ ሲያደርጉ ታይተዋል። እውነተኛ ነቢያት ከእነዚህ ከሚለዩባቸው መለያዎች የቃላቸው ተፈጻሚነት፥ የቃላቸው ከቀደመው የታወቀ የእግዚአብሔር እውነት ጋር መስማማት እና የኑሮአቸው እንደ ቃሉ መሆን ይገኙባቸዋል።*

**ሐስዮት፥ ሒስ፥ ሐያሲ** (criticism, critique) *በአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም የሄድን እንደሆነ ሒስ በጥሬው በሁለት ይተረጎማል። አንዱ ሒስ በደል፥ ገመና፥ የሚያስነቅፍ ነገር፥ ነቀፋ ማለት ነው። ሐያሲም ነቃፊ ከሳሽ ወቃሽ ማለት ነው። ሌላው ትርጉሙ ማሸት፥*

ማፍተልተል፥ ማበራየት፥ መርገጥ፥ ማልፋት፥ ማፍረጥረጥ ማለት ነው። ደግሞም የአሉታ አንቀጽ ሆኖ አንድ ነገር ትክክል አለመሆኑን መናገር፥ ማረጋገጥ ነው። ሒስ በዘመናዊና ሰፊ ትርጉሙ ስህተትን ማሳየትን፥ ማስረዳትን የያዘ ነው። በዘመናዊ የትምህርት መስኮች ከአፍራሽነት ይልቅ ገንቢ በሆነ ሁኔታ በማናቸውም ሁኔታዎች የሚገለገሉበት የግምገማና የእርማት ሂደት ነው። ማሔስ፥ መውቀስ፥ ጥፋትን ማሳየት በየትኛውም ባህል ጤናማ ነገር ነው።

**የመነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች** (Revival and Renewal Movements) ለካሪዝማዊና መሰል እንቅስቃሴዎች የተሰጠ ጠቅላላ ስያሜ። ካሪዝማዊ ንቅናቄ የሚለው ንቅናቄ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም በዚህኛው ስያሜ እየተለወጠ ይገኛል።

**መገለጥ** (Revelation) የተደበቀና የተሰወረ ነገር ወደ ገሃድ መውጣት። ካሪዝማውያን እንደሚሉት ያለ መገለጥ የሚባል ጸጋ ወይም የጸጋ ስጦታ የለም። በ1ቆሮ. 14፥30 የሚገኘው አንዳች ቢገለጥለት የሚለው ሐረግ በጉባኤ አምልኮ ውስጥ በተራ ለሚናገረው ለሌላው በልሳን ተናጋሪ አንዳች ነገር ቢከሰትለት በፊት የሚናገረው ዝም እንዲል ሥርዓትን የሚገልጥ መግለጫ እንጂ ስጦታነቱን የሚያሳይ አይደለም። በካሪዝማዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይህ መገለጥ የሚባለው ነገር ጥበብን ወይም እውቀትን ከመናገር ጸጋ ስጦታ ጋር በማዳበል የመገለጥ ስጦታ እየተሰኘ አንዳንዶች ልክ ከመላ ምት እና ከጥንቆላ ያልተናነሰ ነገር ያደርጉበታል። ብዙውን ጊዜ የሚሠራው ግን የነሲብና የግምት ሥራ ነው። ይህ 'መገለጥ' ግሂደት ወይም ግልጠት ከተባለው የስነ መለኮት ቃል የተለየ ነው።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ፥ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ፥ ዲበመጽሐፍ ቅዱሳዊ** (biblical, unbiblical, extra-biblical) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚባለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቅምህርት ጋር የሚስማማና ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ታማኝ የሆነ ትምህርት ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚጻረር ማናቸውም ትምህርት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። አንድ ትምህርት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚሰኘው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ እውነቶች ላይ ግልጽ ከሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር ሲጻረር ነው። እንዲህ ያለ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ወይም ችግር የሚፈጠረው ብዙውን ጊዜ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ትምህርቱን በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ በማስመሰል ነገር ግን ትክክለኛ ባልሆነ የአተረጓጎም ሂደት በመፍታት ከሚደርሱበት ድምዳሜ የተነሣ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስነ ትርጓሜ ይህ ችግር ከፈቲሖተ ቃል ወይም exegesis የተለየው eisegesis የተባለው አካሄድ ነው። ይህም ወደ ቃሉ ውስጥ ገብቶ ትርጉሙን በማውጣት ፈንታ የራስን የቀድሞ እውቀትና ትርጉም በነባሩ ቃል ላይ መለጠፍ ወይም ከጎኑ መሳግ ነው።

ዲበመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች የትምህርትና የተግባር ምንጫቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ በሆኑ ሌሎች መጻሕፍት ላይ የሚመሠርተ ና ቸው። በአንዳንድ ዘመናዊ ንቅናቄዎች ካሪዝማዊ ቡድኖች ዘንድ ዲበ





መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች አዲስ ስያሜ ተሰጥቶአቸው አንዳንዴ 'የመገለጥ እውቀት' ሌላ ጊዜም 'ሬማ' እየተባሉም ይጠራሉ።

**ሚለር፥ ሚለራውያን** (Millerites) የዊልያም ሚለር ተከታዮች። የዛሬ 150 ዓመታት ግድም በኋላ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የተባሉት ቀድሞ በጀማሪው በዊልያም ሚለር ስም ሚለራውያን ወይም Millerites እየተባሉ ነበር የሚጠሩት። የዚህ ትምህርት ጅማሬ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ ያተኮረ ነበረ። በነበሩበት በኒው ዮርክ በዘመኑ የነበሩ አንዳንድ አስተማሪዎች ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 8 እና 9 በመነሣት የዘመኑንም ቁጥር 2300 ዓመታት በማድረግ ክርስቶስ የሚመጣው በ1843 እንደሆነ አስልተው ገመቱ። ሚለር ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይመጣል ብሉ በ1840ዎቹ መጀመሪያዎቹ ዓመታት አንድ ቀን ወሰነ። ይህ ትምህርቱም ተጋንኖ ተወራና ብዙ ተከታዮችን አፈራ። የተባለውን ቀን መጣና ሄደ፤ ክርስቶስ ግን አልመጣም። ሌላ ቀን ቀጠረ። አሁንም ክርስቶስ አልመጣም። ከዚያ በኋላ እንደገና ሌላ አንድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በርካታ ቀኖች ተቀጠሩ። ሁሉም ከሸፉ። ስህተቱን ተረድቶ ዊልያም ሚለር ቀነ ቀጠሮ መስጠት አደገኛ ስህተት መሆኑን ቶሉ ብሉ ነበር ያወቀው፥ የተጸጸተና የተመለሰውም። በኋላ ሌሎችም ትምህርቶች ተጨምረው የተደራጀ ጉባኤ ሆኖ ቀጠለ። የይሆዋ ምስክሮችን ጨምሮ ሌሎችም በርካታ የታወቁና ያልታወቀቁ ቡድኖች የክርስቶስም ምጽአት ቀን በማስላትና በመገመት ቀጠሮ የያዙ ነበሩ። ሁሉም የተሳሳቱ መሆና ቸውን በተባለው ቀን ክርስቶስ አለመምጣቱ ገልጦታል።

**ማማጥ** (birthing) ከቅርብ ጊዜ፥ በተለይም ከቶሮንቶው ንቅናቄ በኋላ የተጀመረ አዲስ ትዕይንት ወይም manifestation ነው። በተሃድሶና መነቃቃት ልምምዶች በብዛት መታየት ስለጀመረ አሁን ልምምድም ሊሰኝ ይችላል። በማማጥ ትዕይንት ጊዜ ሰዎች ወገባቸውን ይዘው፥ ተንበርክከው፥ ተጋድመው ልክ አንዲት ሴት ልትወልድ ስትል እንደምታምጠው ሆነው በመጮኽ፥ በመወራጨት፥ በማቃሰት በ'ወሊድ' ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። እንዲህ ያለ ልምምድን የሚያበረታቱ አስተማሪዎች እነዚያ ሰዎች በዚያን ጊዜ እነዚያ ሰዎች አንዳች መንፈሳዊ ነገርን እየወለዱ ወይም ለመውለድ በምጥ ውስጥ ናቸው ይላሉ።

**ማኒፌስቴሽን** (manifstation) ቃሉ የእንግሊዝኛ ሲሆን በአማርኛ የሚተካልኝ እኩያ ቃል ስላላገኘሁ ለጊዜው እንዳለ ወስጄዋለሁ። ማኒፌስቴሽን በካሪዝማዊ አምልኮ የሚታወቀውን በዓይን የሚታዩና በጆሮ የሚደመጡ በሰውነትም የሚገለጡ ትዕይንቶች ምንነት የሚገልጥ ቃል ነው።

ትዕይንቶቹ በአንድ ጉባዔ በአንድ ሰው ብቻ የሚከሰቱ አላፊ ልምምድ ሳይሆኑ በብዙዎች ዘንድ የሚታዩና የሚሰነብቱ ወይም የሚከርሙ ስለሆኑ ነው በዚህ ስያሜ የተጠሩት። በጣም የታወቁት ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ። እንደ ሕፃን መንተባተብ፥ እንደ ውሻ መጮህ፥ ማማጥ፥ በመንፈስ መስከር እና መንገዳገድ፥ (አንዳንዶች አምልኮና ዝማሬውን መንፈሳዊ መጠጥ፥ ሰባኪዎችን ደግሞ ጠጅ አሳላፊ እያሉም ይጠራሉ)፥ መንቀጥቀጥ፥ እየነጠሩ መዝለል፥

መንከባለል ወይም በወለል ላይ መንደባለል፥ በቁም መሽከርከር፥ መገንደስ፥ ቅዱስ ሳቅ፥ መወራጨት፥ የማይታይ ካራ ወይም ሰይፍ እንደያዙ ሆኖ መሰንዘርና አጋንንትን እየቆረጡ እየከተፉ የሚዋጉ መምሰል፥ በኃይለኛ ቡጢ እንደተመቱ ኩምትር ጭብጥ ብሉ ማጎንበስ፥ የማይተረጎም ልሳን፥ እሪ ብሉ መጮኽ፥ ወዘተ። ለእነዚህ ትዕይንቶች ማለቂያ የላቸውም። አንዳንዶቹ በአንዳንድ ቦታዎችና ጊዜዎች ሲከስሙ በሌላ ቦታና ጊዜ አዲስ ናቸው።

**ሲንክረቲዝም፥ ቅይጥ እምነት፥ ብፌ ሃይማኖት** (syncretism) ግልጽና ወጥ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ሳይሆን ከየሃይማኖቱ ምቹና ጥሩ መስለው የታዩ ነገሮችን፥ ልምምዶች፥ ዶክትሪኖች ወይም አስተምህሮቶችን በመውሰድ አደባልቆ የራስ ማድረግ። ይህ ዘመን በአጠቃላይ ሲታይ አንድ እምነት ከሌላ እየተቀየጠና እየቀጠነ ዓይነቱም እየበዛ አዳዲስ ትምህርቶችና ልምምዶችም እንደ አሸን እየበዙ የመጡበት ዘመን ነው። ቅይጥነታቸው አንዱ ከሌላው ጋር ለመቻቻል የሚደረገው ሙከራ ቢመስልም ዘመናዊ ስምና መልክ እየተሰጣቸው ከመጡት ምሥራቃውያን ሃይማኖቶች ጋርም ጭምር እስከመቀያየጥ የደረሱ አሉ።

**ስነ መለኮት፥ ነባቤ መለኮት፥ ነገረ እግዚአብሔር** (theology) ሰፋፊ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም መለኮታዊ ትምህርቶችን የሚመረምርና የሚያስረዳ ጥናት ወይም የትምህርት ክፍል። አንዳንድ የስነ መለኮት ትምህርት ጥልቅ ጥናት ለማድረግ በአንድ አቅጣጫ ወይም ክፍል ላይ ብቻ ሊያተኩር ይችላል፤ ለምሳሌ፥ ብሉይ ኪዳናዊ ስነ መለኮት፥ ቅምር ስነ መለኮት፥ ታሪካዊ ስነ መለኮት፥ ወዘተ።

**ስነ ትርጓሜ መጻሕፍተ ቅዱሳት** (hermeneutics) መጽሐፍ ቅዱስ እንደምን መተርጎምና መፈታት እንዳለበት የሚያተኩሩ መሠረታዊ ደንቦችና አቀራረቦችን የሚያስተምር የጥናት ክፍል።

**ቃል እምነት** (word-faith) የዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ዋና ትምህርት የሆነና ቃል የራሱ የሆነና ነገሮችን የመፍጠር ወይም የማጥፋት ውስጣዊ ኃይል አለው የሚል ትምህርት። በዚህ ፍልስፍና ቸው ቃልን አሉታዊና አዎንታዊ ንግግር ብለው እሁለት ይከፍሉታል። እነዚህ ሰዎች ስለ ብልጽግናና ስለ ሌሎች ነገሮችም ሲያስተምሩ ተናጋሪዎቹ ቃልን ተናግረው ሃብትን ወይም ፈውስን ወይም ሌላ ነገር መቀበል እንደሚችሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ አሉታዊ ወይም አፍራሽ ነገሮችን መናገር ችግርና መከራ እንደሚያስከትልባቸው ያስተምራሉ።

**ቅምር ስነ መለኮት** (systematic theology) የስነ መለኮት ክፍል ሆኖ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም መለኮታዊ ትምህርቶችን በየዘርፋቸው የሚያስረዳ ጥናት ወይም የትምህርት ክፍል። በዚህ ጥናት ውስጥ እያንዳንዱ ዐቢይ የትምህርት ዘርፍ ወይም ርእስ ራሱን ችሉ ይተነተናል። ለምሳሌ፥ ስነ እግዚአብሔር፥ ስነ ሰብእ፥ ስነ መላእክት፥ ስነ ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ወዘተ።

**ቅባት** (Aanointing) ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በጥሬ ትርጉሙ ዘይት ወይም ፈሳሽ ነገርን ያመለክታል። ክርስቶስን





በተመለከተ ክርስቶስ ወይም ክሬስቶስ የሚለው ቃል ራሱ ክሪዝማ ወይም ክሪዝማቶስ χρῖσμα, χρῖσματος ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ነው። ክርስቶስ የተቀባው ወይም ከአብ የተላከው መሢሕ መሆኑን ያሳያል። አማኙን በተመለከተ ደግሞ በአጠቃላይ ይዘቱ የመንፈስ ቅዱስን በዚያ ሰው ውስጥ መኖር የሚያሳይ ነው። ስለዚህ በ2ቆሮ. 1፥21፤ 1ዮሐ. 2፥ 20 እና 27 እንደምናየው አማኞች ሁሉ የተቀቡ እንደሆኑ እንረዳለን። ያልተቀባ አማኝ የለም። በካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ግን ቅባት እንደ ብሉይ ኪዳን ክስተትነቱ ልዩ አገልግሎትና የሹመት መግለጫ በመሆን ይተረጎማል። አንዳንዴም እንደ አንድ ዓይነት ጸጋ ወይም ወራጅ ኃይል ተደርጎም ይጠቀሳል። እነዚህ ትክክለኛ ያልሆኑና በልምምድ ላይ የተመረኮዙ ትርጉሞች ናቸው።

**ብልጽግና የብልጽግና ወንጌል፥ የጤንነትና ብልጽግና ወንጌል** (gospel of wealth; health and wealth gospel) ማንም በክርስቶስ የሚያምን ሰው ኃብታምና ጤነኛ፤ እጦትና ሕመም ከቶም የማይነካው መሆን አለበት የሚል ትምህርት ነው። የዚህ ትምህርት መንደርደሪያዎች ጥቂት የብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ከዐውዳቸው ተነቅለው የተገመዱ ጥቅሶች ናቸው። የብልጽግና ወንጌል የዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ታዋቂ የሆነ የክርስቲያን ሃብታምነቱ የትክክለኛ ክርስቲያንነቱ ወይም በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የመሆኑ ምልክት ሲሆን ድህነቱ ደግሞ የእምነት ማጣቱ ወይም የኃጢአቱ ምልክት ነው የሚል አስተምህሮት ነው። ታዋቂዎቹ የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎችና አራማጆች የሚበለጽጉት ግን ከሚያስተምሩአቸውና ትምህርታቸውን ከሚቀበሉት የዋሆች ኪስና ቦርሳ ከሚያገኙት ከልክ ያለፈ ንዋይ ነው።

**ተዋሕዶ** (Monophysitism) ከስነ መለኮት አንጻር ተዋሕዶ ማለት አንድ ገጽታ፥ አንድ ባሕርይ ማለት ሆኖ የክርስቶስን ባሕርይ ለማሳየት የዋለ ቃል ነው። በመደበኛው ወንጌላዊ እምነት ውስጥ የሚታወቀው ክርስቶስ ፍጹም አምላክ፥ ፍጹም ሰው ሁለት ባሕርይ በአንድ አካል ሲሆን በተዋህዶ አስተምህሮት ደግሞ መለኮታዊና ሰብአዊው ባሕርያት በአንድ መለኮታዊ ባሕይር አንድ የተዋሃደ ባሕርይ ብቻ፥ እሱም መለኮታዊ፥ እንዳለው የሚያሳይ ነው። በተዋሕዶ እምነት የሚታየውም በኬልቄዶን ጉባዔ የተወገዘው አስተምህሮ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ውስጥ በወልድ ማንነት ላይ ሦስት ያህል የተለያዩ ግን ብዙም ያልተራራቁ አመለካከቶች አሉ። ተዋሕዶ የሚባለው አንደኛው ሲሆን እሱም የጸና ው በቦሩ ሜዳ በዐፄ ዮሐንስ እና በንጉሥ ምኒልክ ፊት በተደረገው ክርክር አሸናፊ የሆኑት ተከራካሪዎች በመርታታቸው መሆኑ በታሪክ ይገኛል።

**ኀሊዎተ እምነት** (apologetics) ማናቸውንም እምነት፥ ወይም በዚህ አካሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ ክርስትናን ከሐሰት ትምህርቶችና ልምምዶች መከላከልና መመከትን የሚገልጥ ስያሜ ነው። ቃሉ ለክርስትና ብቻ ሳይሆን ለሌሎች እምነቶችና ለስህተት እምነቶችም ጭምር ሊውል ይችላል። ለምሳሌ፥ የታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና መካቾች ኀለውተ ክርስትና Christian Apologists ሲባሉ

የስህተት ትምህርቶችን ለመመከት የሚታገሉ ሰዎች Cult Apologists ይባላሉ። ቃሉ እስከዚህ ሰፊ ነው። ኀሊዎት ወይም ሐሊዎት መጠበቅን፥ በተለይም በሌሊት መከላከልን ያመለክታል። ይህ ኀሊዎተ እምነት የተሰኘው ስያሜ በአንዳንድ ጽሑፎች ዐቃቤ እምነት ወይም ዐቃቤ ክርስትና ተሰኝቶአል።

**ኃይል የወንጌል ስርጭት** (power evangelism) ወንጌል ሲሰበክ ተአምራትና ምልክቶች ካልታዩበት ሙሉ ወንጌል ሊባል አይችልም የሚል ትምህርት ነው። ተአምራትን ከመጠማትና ከመፈለግ ስህተት ጋር የተያያዘም ትምህርት ነው። ፒተር ዋግነር የተባለው የዚህ ትምህርት ጀማሪ ትምህርቱን የቀመረው ስለ ወንጌል ስርጭት በሚያስተምርበት ጊዜ ተአምራት በሚከሰቱበት ወይም ምልክቶች በሚታዩበት ጊዜ ሰዎች ያንን አይተው በብዛት ወደ እምነት እንደሚመጡ አስረጅና ድጋፍ በማድረግ ነው። በእርግጥ ትክክለኛና ጤናማ ተአምራትና ምልክቶች ከጌታ ዘንድ ቢደረጉ ሰዎች ወደ እውነት ሊጠጉ ይችላሉ፤ ወደ እምነት የሚያመጣቸው ግን ምልክት ሳይሆን መስማት ነው። እምነት የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነውና። ምልክት ካልታየ ደግሞ አንድ የወንጌል ስርጭት እንደከሸፈና ምልክት ከታየ እንደስኬታማ ከተቆጠረ መለኪያው አሳሳች ሊሆንም ይችላል፤ ምልክት ሁሉ በእግዚአብሔር አይደረግምና።

**ኀሊናዊ** (subjective) የአንድን ነገር ትክክለኛ መሆን ወይም ያለመሆን በቃሉ ላይ ሳይሆን በሰብአዊ ልምምድ ብቻ ላይ በመመስረት የሚወሰን ዳኝነት። የዚህ ልምምድ ስሕተት ዳኝነቱ ከሰው ወደ ሰውና ከጊዜም ወደ ጊዜ መለያየቱና ሚዛናዊ ያለመሆኑ ነው። ስለዚህ ከነባራዊውና ከማይለዋወጠው (objective) እውነት የራቀ ነው። ለክርስቲያን ይህ ነባራዊ እውነት ቃሉ ነው። አንድ ትምህርት፥ ልምምድ፥ ድርጊት፥ ወዘተ፥ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን መፈተሻው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው መሆን ያለበት።

**ነጻ፥ ከቤተ እምነት ነጻ ቤተ ክርስቲያን** (Free Churches Movement) ከሌሎች ነባር አብያተ እምነት ነጻ የሆነች ቤተ ክርስቲያን የመመሥረት ንቅናቄ። አንዳንዶቹ ከወንጌል ስርጭትና ከቤተ ክርስቲያን ተከላ ጋር ተያይዘው የተመሠረቱ ሲሆኑ ብዙዎቹ ነጻ አብያተ ክርስቲያናት ከመሪዎች ወይም ቆርቋሪዎች ከተጠያቂነት ነጻ ለመሆን መፈለግ የተነሣ የተጀመሩ ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛውን ጊዜ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት ተለይተው በመውጣት ነው የሚጀመሩት። ከኃላፊነት ተጠያቂነት ብቻ ሳይሆን ከአስተምህሮትና ስነ መለኮት ተጠያቂነትም ነጻ ስለሚሆኑ ለስህተት የተዳረጉና አንዳንዴም ከምሥረታቸው ጀምሮ በስህተት ትምህርት ወይም ልምምድ ላይ የተገነቡ ናቸው።

**ኑፋቄ** (sect) በጥሬው የሚነፍቅ፥ የሚከፍል፥ የሚገምስ የሚሰነጥቅ ማለት ነው። የስህተት ትምህርትነትን በተመለከተ ደግሞ ከስሕተት ትምህርትነቱ ሌላ የጥርጥር ዘርን በመዝራት ከአንድ ነባር እምነት ወይም ቤተ ክርስቲያን መርጦና ገምሶ መውሰድን ይገልጣል።





አንዳንድ ጸሐፊዎች ኑፋቄን cult ለሚለው ቃል አቻ አድርገው ይወስዱታል። ቃሉ ግን ከcult ይልቅ ለsect ይቀርባል።

**ንስጥሮስ፥ ንስጥሮሳውያን** (Nestorianism) ንስጥሮስ በተባለ ካህን የተጀመረ በ5ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት የነበረ ክርስቶስ ሁለት አካሎች ነበሩት የሚል ትምህርት። በ431 ዓ. ም. በኤፌሶን በተደረገው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባዔ ተወገዘ።

**አርዮስ፥ አርዮሳውያን** (Arianism) አርዮስ በተባለ በእስክንድርያ የነበረ አገልጋይ የተጀመረ ክርስቶስ ያልነበረበት ዘመን ነበረ የሚል ትምህርት። የአርዮሳውያን ትምህርት በ3ኛው መቶ ምዕት ዓመት ተጀምሮ የክርስቶስን አምላክነት ለማይቀበሉ፥ ፍጡር ነው ለሚሉ እንደ ይሆዋ ምስክሮች የመሰሉ የሐሰት ትምህርቶች ሁሉ መሠረት የሆነ ስሕተት ነው። በ325 ዓ. ም. በኒቅያው ጉባዔ ተወገዘ። በዚህ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የተነሳው የይሆዋ ምስክሮች ትምህርት የአርዮስ ስህተት ትንሳኤ ነው።

**አስተምህሮት** (doctrine) መሠረታዊና ምድብ የክርስትና ትምህርት። ስነ መለኮት ሰፋፊና ዋና ዋና በሆኑ የነገረ መለኮት ርእሶች ላይ ሲያተኩር አስተምህሮት እስከ ታናናሽና ንዑሳን ርእሶች ድረስም ተሸንሽኖ ይበተናል። አስተምህሮት ወይም ዶክትሪን በራሱ በጣም ጤናማና አስፈላጊ ነገር ነው። አንድ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ ትምህርቶች መረዳት ያስፈልገዋል። ያለዚያ በቀላሉ በስሕተት ትምህርቶች ሊወሰድ ይችላል። ባለማወቅ አንዳንዶች ዶክትሪንን የመንፈሳዊነት ተቃራኒ እንደሆነ አድርገው ያጥላሉታል። ይህ በካሪዝማዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ይታያል። ግን ይህ ማጥላላት ወደ ስሕተት የመሄጃው አቋራጭ መንገድ ነው።

**አቡልናርዮስ፥ አቡልናርዮሳውያን** (Appolinarians) አቡልናርዮስ በተባለ ሰው የተጀመረ በ4ኛው መቶ ምዕት ዓመት የነበረ ትምህርት። የእርሱና የተከታዮቹ ትምህርት የክርስቶስን መለኮትነት ይቀበላል፤ ሆኖም፥ ሰብእናውን በከፊል ይክዳሉ፤ በረቂቅ ትምህርታቸውም ቃል ወይም ሎጎስ የክርስቶስን ሰብአዊ መንፈስ ተክቶታል የሚሉት ትምህርት አላቸው። ይህ ስሕተት በ680 ዓ. ም. በኬልቄዶኑ ጉባኤ የተወገዘ ነው።

**አብርሆት** (illumination) መንፈስ ቅዱስ ተጽፎ የተጠናቀቀውን ቃል፥ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ለአንባቢዎቹ ወይም ለሰሚዎቹ ሊያስረዳቸው ወይም ሊያበራላቸው የሚችልበት አገልግሎት። ይህ የአብርሆት ሥራ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ውስጥ የሚሠራው የእግዚአብሔርን እውነት የማሳየት፥ የመከሰት ወይም የማስረዳት ተግባር ነው። ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና ማንም ሰው ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለመንፈሳዊ ነገር በሥጋዊ አእምሮው ብቻ መረዳት አይችልም። አንድ ሰው ክርስቶስን ሲቀበልና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ መኖር ሲጀምር ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ ያ ሰው ቃሉን በሚያነብበት ጊዜ ሊኖርበት

የሚገባውን እውነት ማስረዳት ወይም መከሰት ነው። ይህ የማብራት፥ የማስረዳት ሥራ ነው አብርሆት።

**አንድምታ** የትርጓሜ ስልት ሆኖ አንድን ሐረግ ወይም አሳብ በብዙና የተለያዩ መንገዶች የመፍታት መንገድ ነው። ይህ የተሳሳተ የድርብርብ አተረጓጎም ስልት ነው። ይህ አንድምታ ወይም ድርብርብ ትርጓሜ 'ይህ ሲባል አንድም እንዲህ፥ አንድም፥ እንዲያ፥ አንድም ደግሞ እንዲያ እያሉ አንድን ክፍል በብዙው መተርጎም ነው። ምናልባት ትንቢት ብቻ በድርብ ሁኔታ ሊፈጸም፥ ማለትም መጀመሪያ በከፊል ኋላም በሙሉ ሊፈጸም የሚችልበት ሁኔታ ይኖር ይሆናል፤ ያም ቢሆን ፍጻሜው ላይ ነው እንጂ ትርጓሜው ላይ አይደለም። ከዚያ ሌላ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በአንድምታ ድርድር የሚፈቱበትና ፍቺውም ከብዙ መሃል በመላ የምናገኘው አይደለም። አንድ ክፍል የሚያስተላልፈው አንድን ነገር ብቻ ነው። ያም አንድ ነገር ጸሐፊው ለተቀባዮቹ ወይም ለአንባቢዎቹ ሊል የፈለገው ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ሁሉ ሰምና ወርቅ አይደለም። በምሳሌያዊ አተረጓጎም የምንረዳቸው ክፍሎችም የሚናገሩት አንድ ትርጉምን ብቻ ነው እንጂ በመሰለኝ ሰነጣጥረን በብዙ የምንፈታው አይደለም። ለአንዳንድ ሰባኪዎች እንደሚመስላቸው የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ቃል ስለሆነ ብዙ ኀብር ያለውና በሰባት መንገድ የሚፈታ አይደለም። መልእክቱ የእግዚአብሔር ቢሆንም ቋንቋ የሰው ቋንቋ ነው።

**አውጣኪ፥ አውጣኪያውያን** (Eutychianism) አውጣኪ በተባለ ሰው በ5ኛው መት ምዕት ዓመት የተቀመረ በክርስቶስ ባህርይ ላይ የተመረኮዘ የስህተት ትምህርት። ክርስቶስ ሙሉ ሰውም ሙሉ አምላክም ሳይሆን የተዋሃደ አንድ ባህርይ ነው በዚህ ተዋሕዶም መለኮታዊው ሰብዓዊውን ውጦታል የሚል ትምህርት ነው። ተዋሕዶ ከዚህ የመነጨ ነው። በ451 ዓ. ም. በኬልቄዶኑ ጉባኤ ተወገዘ።

**አጶቅሪፋ** (apocrypha) ጥሬ ትርጉሙ የተሰወረ፥ ግልጽ ያልሆነ ማለት ነው። በላቲን ቩልጌት ወይም የካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የተሰገሰጉ ኢቀኖናውያን መጻሕፍት። አንዳንዶቹ፥ እየራሳቸው መጻህፍት ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ የመጽሐፍ ቅጥያ ናቸው። በ1546 ዓ. ም. ነው በትሬንት በተደረገው ጉባኤ የላቲን ቀኖና ውስጥ የገቡት እንጂ ከዚያ በፊት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አልነበሩም። በብሉይ መጻሕፍት ውስጥ ይሰግሰጉ እንጂ በአይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም እኛ ብሉይ ኪዳን በምንለው ውስጥ ግን ከቶም አይገኙም። የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ስምንት በብሉይ፥ ሰባት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመጨመር 81 መጻሕፍት ያሉት መጽሐፍ አላት። እነዚህ መጻሕፍት በቀኖና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልገቡ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በይሁዳ መልእክት ውስጥ አንድ የአጶቅሪፋ መጽሐፍ ተጠቅሶ ይገኛል። ያም መጽሐፈ ሄኖክ የተባለው ነው። ይሁዳ የጠቀሳቸው እነዚህ የአጶቅሪፋ ጽሑፎች በእርሱ መጠቀሳቸው እነዚህን መጻሕፍት ቀኖናዊ አያደርጋቸውም። ይህ መጽሐፍ በሄኖክ እንደተጻፈ ነው መጽሐፉን የሚቀበሉት ክፍሎች የሚናገሩት። ይሁን





እንጂ እስከ 100 ዓመተ ዓለም ድረስ መኖሩም እንኳ አይታወቅም ነበር፤ ወይም ያልነበረ መጽሐፍ ነው። ሆኖም አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመናት የታወቀ ጽሑፍ ነበረ። በቀኖና መጻሕፍተ ቅዱሳት ውስጥ ያልገባ መሆኑ በውስጡ እውነት የለም ማለት አይደለም። ነገር ግን መጽሐፍ ብቻ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ አይደለም።

**አፊዎት፥ አፊዎተ መለኮት፥ እስትንፋሰ እግዚአብሔር** (inspiration) መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንደመነጨ ወይም ሰዎች ቃሉን የጻፉት በእግዚአብሔር መንፈስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እንደሆነ የሚያስረዳ አሳብ ነው። በ2ጴጥ. 1፥21 ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው እንደተናገሩ የተጻፈበት ቃል ዋናው አስረጅ ነው።

**ኢስጦኢኮች፥ የኢስጦኢኮች ትምህርት** (Stoicism) የዓለማዊ መጀመሪያ ትምህርት ወይም የማናቸውም ትምህርት፥ የትምህርቱ የመጀመሪያ ንጥረ ነገር ማለት ነው፤ ገላ. 4፥3 እና 9፤ ቆላ. 2፥8 እና 20፤ ዕብ. 5፥21 እንዲሁም ሐዋ. 21፥24። አንድ ዓይነት ወግ ወይም ትምህርት ወይም ፍልስፍናን በመቀመር ያንን ተጨንቆና ተጠቦ በመጠበቅ ለመኖር የሚተጉ ሰዎች ማኅበርም ነው ሐዋ. 17፥18።

**ኢየሱስ ብቻ** (Jesus Only) በአሜሪካ ከጴንጤቆስጣውያን ንቅናቄ ውስጥ በ1920ዎቹ መጨረሻ ተለይተው በመውጣት የጴንጤቆስጣውያን አንድነት ማኅበር (United Pentecostal Church) በሚል ስያሜ ራሳቸውን የጠሩ፥ አስተምህሮተ ሥላሴን የማይቀበሉ፥ በኢየሱስ ስም ብቻም የሚያጠምቁ ማኅበራት። በኢትዮጵያ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የምትባለው ከዚህ አንድ ናት።

**ኤሲናውያን** (Essenes) ከአይሁድ ወገን የሆኑና ከዘመናቸው ፈሪሳዊና መንፈሳዊነት ከጎደለው ሃይማኖታዊ ሰው ሠራሽ ሕግጋት ርቀው በበረሃ ቃሉን እያጠኑና እየጻፉ ይኖሩ የነበሩ ማህበራት። በርካታ ጥንታውያን ጽሑፎች የተገኙባቸው የቁምራን ዋሻዎች የእነዚህ ሰዎች መኖሪያ እንደነበሩ ይገመታል።

**ኤብዮናውያን** (Ebionites) በ2ኛው መቶ ምዕት ዓመት የነበሩ ኢየሱስ የዮሴፍና የማርያም የተፈጥሮ ልጅ ብቻ እንጂ ምንም መለኮታዊነት የለውም የሚል የኑፋቄ ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ማኅበር። መሐመድ ስለ ክርስቶስ የተረዳው ከእነዚህ ሰዎች ይመስላል።

**እምነት፥ የእምነት ፈውስ** (faith healing) በካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በስፋት የሚደረግ አንድ ሰው ከማናቸውም አካላዊ ሕመም የሚፈወስበት ልምምድ። ፈውስ በጤናማ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ስጦታ ሲሆን ይህን ልዩ የሚያደርገው ዋና ነጥብ የፈውስ ስጦታ አለው የሚባለው የሚጸልየው ሰው ሲሆን ለመፈወስ ግን የበሽተኛው እምነት የግድ ተፈላጊ መሆኑ ነው። ፈውሱ ሳይከሰት ሲቀር ተወቃሹ እምነት ያጣው ሕመምተኛው ሰው ነው እንጂ የፈውስ ስጦታ አለኝ ባዩ አይደለም።

**ክልት፥ መናፍቅ** (cult, heresy) *ክልት በሰፊ ትርጉሙ ማናቸውም የአምልኮ ሥርዓትን እስኪይዝ ድረስ ሰፊ ቃል ነው። ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና አንጻር በአጭሩ ሲገለጥ ግን አንደኛ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ተጻራሪ ስነ መለኮትን የሚያስፋፋ ትምህርት ነው፤ ሁለተኛ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ላልሆነና የሰዎችን መንፈሳዊና ስነልቡናዊ ታዛዥነት ያለልክ ለሚፈልግ የሥልጣን ጥም ማጎብደድን የሚያስፋፋ ከታወቁት የዓለም ሃይማኖቶች ያልተመደበ ማናቸውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ነው። ክልት በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተመሠረተ የሚናገር የተሳሳተ ሃይማኖታዊ ቡድን ሆኖ ነገር ግን ባህርያቱን የሚገልጡት ትምህርቶቹ ከክርስትና መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር የሚቃረኑ፤ የኑሮ መለኪያቸው ከክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ጋር የሚቃረን፤ እንዲሁም የአመራር መለኪያዎቻቸው ከክርስቲያናዊ የአመራር መስፈርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው*

*ኑፋቄ (sect) በጥሬው የሚነፍቅ፥ የሚከፍል፥ የሚገምስ የሚሰነጥቅ ማለት ነው። የስህተት ትምህርትነትን በተመለከተ ደግሞ መናፍቅነት፥ ጥርጥር፥ ከፊሉን አምኖ ከፊሉን መጠርጠር ወይም መካድ ማለት ነው። (ኪዳነ ወልድ፥ 645-6) ከስሕተት ትምህርትነቱ ሌላ የጥርጥር ዘርን በመዝራት ከአንድ ነባር እምነት ወይም ቤተ ክርስቲያን መርጦና ገምሶ መውሰድን ይገልጣል። አንዳንድ ጸሐፊዎች ኑፋቄን cult ለሚለው ቃል አቻ አድርገው ይወስዱታል። ቃሉ ግን ከcult ይልቅ ለsect ይቀርባል።*

*Heresy የሚለውን አሳብ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሐራጥቃ ይለዋል። ሲተረጉመውም ጠዋየ ሃይማኖት፥ ባህሉና ትርጓሜው ከመጽሐፍ ከንባብ የማይገጥም፥ መጻሕፍት እወ ያሉትን አልቦ፥ አልቦ ያሉትን እወ የሚል፥ የርሱን ሐሳብ ብቻ የሚከተል... ይለዋል። (ኪዳነ ወልድ፥ 462።) ቃሉ ከግሪኩ ኤሬቲክ የተወሰደ ነው። የግሪኩ ቃል አይሬቲኮስ (αἱρετικός) የሚል ሆኖ αἱρετίζω ከሚል ግስ ወይም αἵρεσις ከሚል ስም የወጣ ቃል ነው። ትርጓሜውም መምረጥ የሚል ዋና ቃል ሆኖ መርጦ ወይም ለቅሞ መነጠልን፥ ጎራ ወይም ቡድን መመሥረትን የያዘ አሳብ ነው። ይህን የሚያደርግ ማናቸውም ትምህርት በዚህ ስም ሊጠራ ይችላል። በገላ. 6፥20 የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ይህ ነው። ኑፋቄ ወይም መናፍቅነት የሚባለውም ከዚህ የሚቀራረብ ነው። Heresy የተሳሳተ ትምህርቱን ክልት ደግሞ ድርጅቱን ወይም ሃይማኖታዊ መዋቅሩን በመላው ሊገልጥ ይችላል።*

*የስሕተት ሃይማኖቶችን*

ካሪዝማ (charisma) በሰፊና ዓለማዊ ትርጉሙ ካሪዝማ ማለት የአንድ ሰው የተለየ ችሎታ ወይም ሞገስ ማለት ነው፤ ብዙውን ጊዜ ለመሪነት የሚሰጥ ቅጽልም ነው። በመንፈሳዊ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ ካሪዝማ *χάρισμα, χάρισματος* ከሚል የአዲስ ኪዳን ግሪክ ስርወ ቃል የመነጨ ነሆኖ ነፃ ቸርነት፥ ነፃ ስጦታ፥ ከመለኮት የተቸረ ጸጋ፥ የጸጋ ስጦታ ማለት ነው።





**ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ** (Charismatic Movement) *ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ወይም ንቅናቄ ሰፊ የሆነውን ካሪዝማ ወይም የጸጋ ስጦታ የሚል ቃል ይያዝ እንጂ በጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ላይ ሳይሆን በአንድ ስጦታ፥ ማለትም፥ በልሳን ላይ ያተኮረ የልሳን ንቅናቄ ነው። እንቅስቃሴው በልሳኖች የመናገር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖርና ሊታይ የሚገባው ልምምድ ነው የሚሉ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያኖች እና ንቅናቄዎችን የሚያቅፍ ነው። እነዚህ በጠቅላላው ከመጀመሪያው ወይም ኦርጂናሌው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ያልመነጩ ተቋሞች እና ቤተ እምነቶች ክፍሎች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ ደግሞ ካሪዝማ የጸጋ ስጦታ ማለት ነው። ማናቸውም መንፈስ ቅዱስ የሚያድለው በጸጋ የተገኘ ስጦታ ሁሉ ካሪዝማ ነው። እንደዚህ ትርጉም ከሄድን ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ሁሉ ቢያውቀውም ባያውቀውም፥ ቢለማመድና ቢያገለግልበትም ወይም ሳያውቀው ቀርቶ ይዞት ቢኖር የጸጋ ስጦታ ወይም ካሪዝማ አለው። ስለዚህ ነው ከላይ ካሪዝማዊ ንቅናቄ የልሳን ንቅናቄ ነው ያልኩት። ካሪዝማዊ እንቅስቃሴዎች ከትምህርት ይልቅ ልምምድ ላይ ስለሚያተኩሩ ብዙውን ጊዜ አወዛጋቢና የስህተት ትምህርቶች ይመነጬባቸዋል።*

**ዐውደ ወጥነት** (out of context) *በስብከት ወይም ትምህርት ውስጥ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከታሪካዊና ስነ ጽሁፋዊ ከባቢው በመነጠል ጸሐፊው ያላለውን ነገር ወደሚልበት ወይም በዐውዱ ውስጥ ቢጠና ጥቅሱ ሊል ወደማይችለው መድረሻ የማምጣት ሂደት።*

**የይሆዋ ምስክሮች** (Jehovah's Witnesses) *ከቀዳሚው የአድቬንቲዝም ንቅናቄ ተገንጥሎ የወጣና ከ1910ዎቹ በኋላ ተጠናክሮ የተደራጀ ማኅበር። አስተምህሮተ ሥላሴን የሚክድና በክርስቶስ ማንነት ላይ ያለው ትምህርት ከአርዮስ ትምህርት ጋር አንድ የሆነ፥ ክርስቶስን ፍጡር ብቻ የሚል፥ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ በርካታ አወዛጋቢና የተሳሳቱ ቀኖችን በመወሰን የተጠባበቀ፥ ሌሎችም በርካታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ ትምህርት ያፈነገጡ ትምህርቶችን ያቀፈ ድርጅትና የድርጅቱ ተከታዮች።*

**ገለጣ ስብከት** (expository preaching) *ገለጣ ማለት ከተጻፈው ቃል ውስጥ እውነትን አውጥቶ መናገር ወይም ማሳየት ማለት ነው። የእኛን አሳብ ወደ ቃሉ ውስጥ በማስገባት እኛ የፈለግነውን እንዲል ማድረግ ሳይሆን በውስጡ የተጻፈውን አሳብ ጥንቃቄ በተሞላ መንገድ የጸሐፊውን አሳብና የመጀመሪያዎቹ የቃሉ ተቀባዮች እንደሚረዱት አድርጎ ለመረዳት መመርመር ነው። በስብከት ወይም ትምህርትም ሆነ በጽሑፍ ረገድ ገለጣ ከማብራሪያ ወይም ትንተናና ሐተታ መጻሕፍት (commentaries) ይለያል። ማብራሪያ ከቃሉ ውጪ ታሪካዊ ሰነዶችን ሁሉ ሰመረምር ገለጣ ግን ከቃሉ ውስጥ ይቆያል። ይህ የቃሉን ዐውድም ይዘትም ሳናስተጓጉል መጨበጥ እንድንችል ያደርገናል። ገለጣ በስብከትም ሆነ በትምህርት መልክ ሊቀርብ ይችላል። የገለጣ ዋና ትኩረት የተጻፈው የተወሰነ ክፍል ላይ ነው።*

**ግሂዶት፥ ግልጠት** (revelation) *እግዚአብሔር ራሱን ለማሳወቅ፥ ለመግለጥ የተጠቀመባቸው መንገዶች። ግሂዶት በሁለት ይከፈላል፤*

የመጀመሪያው ጠቅላላ ግሂደት እግዚአብሔር ማንነቱን በተፈጥሮ፥ በሰው ባሕርይ፥ እና በታሪክ ውስጥ የገለጠባቸው ሁኔታዎች ናቸው። ማንም ሰው እነዚህን ነገሮች ቢመረምር ስለ እግዚአብሔር ኀልውና መረዳት አይሳነውም። ሁለተኛው ልዩ ግሂደት ነው። ይህ ከጠቅላላ ግሂደት በጠለቀ ስለ እግዚአብሔር መረዳትን የሚሰጥ ነው። ልዩ ግሂደት በአጭሩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለ ራሱ የገለጠበት ጽሑፍ በመሆኑ ስሕተትና እንከን የሌለበት፥ አዳኝ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑንና የደኅንነትም መንገድ ምን መሆኑ የተጻፈበት መጽሐፍ ነው።

**ግኖስቲኮች** (Gnostics) *ኖስቲክ እየተባሉም ይጠራሉ። ግኖሲስ ወይም እውቀት ከሚል የግሪክ ቃል የወጣ ስያሜአቸው እንደሚያመለክተው ትምህርታቸው ከልዩ እውቀት ጋር የተቆራኘ ነው። መቼና እንዴት እንደተጀመረ በቂ መረጃ ባይኖርም ይህ ትምህርት ወይም ንቅናቄ ቤተ ክርስቲያን ገና ለጋ በነበረችበት የመጀመሪያው ምዕት ዓመትም ነበረ። ከትምህርቶቻቸው መካከል ጥቂቶቹ ደኅንነት በኢምነት ሳይሆን በልዩ እውቀት ወይም ግኖሲስ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፥ ዓለምም ሆነች ሁሉ ነገር ቁስ አካልና መንፈስ ብቻ እንደሆኑ፥ ቁስ አካል በሁሉ መልኩ ክፉ፥ መንፈስ ደግሞ መልካም መሆኑ፤ ስለዚህ ሥጋን እንደ እስር ቤት በመቁጠር ማናቸውም አካላዊ ነገሮችን ሁሉ መጥላት፤ የሕይወት ዋና ግብ ከዚህ እስር ቤት ከሆነ አካል ወጥቶ ኀዋን ዘልቆ ከእግዚአብሔር ጋር መዋሃድ መሆኑ፤ ሌሎችም ጥቂት ያልሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳነት የራቃቸው ትምህርቶች አሉአቸው።*

**ጴንጤቆስጤ፥ ጴንጤቆስጣዊ** (Pentecost, Pentecostal) *ጴንጤ ቆስጤ በዓለ ኀምሳ ማለት ሲሆን የብሉይ ኪዳኑ ሰባቱ ሱባዔ በዓል ነው። ይህም ከፋሲካ በኋላ ከአርባ ዘጠኘኛው ቀን ቀጥሎ የሚከበር በዓል ነው። መንፈስ ቅዱስ በይፋ በኢየሩሳሌም የወረደው በዚህ ቀን ነበረ።*

*ጴንጤቆስጣዊ የሚለው ቅጽል ደግሞ እንደ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ዘርፍና ልምምድ በታሪክ ውስጥ የታየ ክስተት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት ዕለት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢኖርም ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ እንደወረደበት ቀን ያለው ልምምድ ዛሬም ይደገማል በማለት ይህን የሚያራምድ እንቅስቃሴ ነው። እንዲህ የመሰሉ ልምምዶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ቢኖሩም እንደ እንቅስቃሴ የተከሰተው ግን ከቤተ ክርስቲያን ተሃድሶው ዘመን በኋላ ነው። ይህ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቃውንት ዘንድ እሁለት የሚከፈል ነው። የመጀመሪያው ሁነኛው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ (classical pentecostalism)፥ ሲሆን ሁለተኛው ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ (neo-pentecostalism) ይባላሉ። የመጀመሪያው ንቅናቄ ተሐድሶውን ተከትሎ የታየው ቤተ ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር የተዘጋች ሳትሆን ንቁ መሆን እንዳለባትና የጸጋ ስጦታዎችም ህያው እንደሆኑ ያስተማረ ነው። ሁለተኛው ንቅናቄ ደግሞ ከዚህ ካለንበት ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተጀመረና በክፍለ ዘመኑ አጋማሽ ላይ ከታየው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ጋር ተዳብሎ ከጸጋ ስጦታዎች በጥቂቱ፥ እንዲያውም በአንዱ ብቻ፥ ማለትም በልሳኖች በመናገር፥ እንዲሁም ሌሎች አዳዲስ ትምህርቶችና ልምምዶች ላይ ያተኮረ ንቅናቄ ነው።*





**ፈውስ፥ ስሜታዊ ፈውስ** (psychosomatic healing) *በዘመናዊዎቹ የፈውስ ፕሮግራሞች ውስጥ የሚታይ ለተፈዋሾቹ አካላዊ ፈውስ የሚመስላቸው፥ ነገር ግን አካላዊ ያልሆነና ስሜታዊ ብቻ የሆነ ፈውስ። ተፈዋሾቹ እንደሚፈወሱ ስለሚጓጉና ስለሚጠብቁ፥ ፈዋሾቹም የተወሳሰበ ቀመር ስለሚጠቀሙና በዚህ ጉጉትና ጥበቃ ውስጥ የእውነተኛውና የውሸታሙ ድንበር ጠፍቶ ስለሚደባለቅ ሕመምተኞቹ የተፈወሱ ይመስላቸዋል። የተለመደና ከዚያ በፊት የሰሙትን አንድ ዓይነይ ምልክትም ስለሚጠብቁ በዚያ የተወጠረ ሁኔታ ውስጥ ያ የተፈጸመም ይመስላቸዋል። ስለዚህ ሳይፈወሱ የተፈወሱ መስሉአቸው አንዳንዶቹ ወደ መድረክ ወጥተው ይመሰክራሉ፤ አንዳንዶች መድኃኒታቸውን ይጥላሉ። ሲረጋጉ ግን ፈውሱ የለም፤ ሕመሙ ግን እዳሮው ስፍራ ነው።*

# ዋቤ መጻሕፍት


የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ፥ ከ፲፱፻፵፮ ዓመተ ምሕረት ዕትም The Bible in Amharic, UBS, 1962. ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት ነው።

በቀለ ወልደኪዳን፥ ሪቫይቫል፥ ኢትዮጵያ እና የመጨረሻው መጨረሻ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፥ ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ፥ ኃ፥ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ ፲፱፻፷፭ ዓ. ም.።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ ፲፱፻፸፫ ዓ. ም.።

የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ኅብረት በጀርመን፥ ዓመታዊ ኮንፈረንስ ቪድዮ፥ 2000።

ጸጋ የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ቫንኩቨር፥ ካናዳ፥ የአምስት ቀናት የኮንፈረንስ መልእክቶች፤ June 2001።

Ankerberg, John and Weldon, John. *Cult Watch*, Harvest House Publishers, Eugene, OR. 1991.

Anderson, Neil T. *The Bondage Breaker*, Harvest House Publishers, Eugene, OR, 1990.

Appel. *Cults in America*,

Arthur, Kay. *How to Study Your Bible*, Harvest House Publishers, Eugene, OR. 1994.

Bakker, Jim with Abraham, Ken. *I Was Wrong*, Thomas Nelson Publishers, Nashville, TN. 1996.

Bowman, Robert M. "A Biblical Guide to Orthodoxy and Heresy Part One: The Case For Doctrinal







Discernment," Christian Research Journal, Summer 1990.

Branham, William. *Footprints on the Sands of Time: The autobiography of William Marrion Branham*, Part Two, Spoken Word Publications, Jeffersonville, IN., 1975.

Burgess, Stanley M. and McGee, Gary B., editors, *Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements*, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI.,

Canright, D. M. *Seventh Day Adventism Renounced*, Baker Book House, Grand Rapids MI. 1961.

Charisma News, "Gold Dust Phenomenon Stirs Up Questions Among Charismatics," Sep. 9, 1999.

Christian Research Journal, CRJ0063A, (www.equip.org.) 1994.

Copeland, Kenneth, *Following the Faith of Abraham I*, Fort Worth: Kenneth Copeland Ministries, 1989, audiotape #01-3001.

DeHaan II, Martin R. *How To Identify Dangerous Religious Group*, RBC, Grand Rapids, MI. 1994.

Enroth. *The Lure of the Cults*,

Fee, Gordon, and Stuart, Douglas. *How To Read The Bible For All Its Worth*, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI. 1982.

Galanter, Mark. *Cults, Faith, Healing and Coercion*, Oxford University Press Inc., N.Y., 1989.

Geisler, Norman L. *Baker Encyclopedia of Christian Apoligetics*, Baker Books, Grand Rapids, MI. 1999.

Hall, Franklin. *The Return of Immortality*, Hall Deliverance Foundation, Phoenix, AZ., 1976.

Hall, Franklin. *Atomic Power With God Through Fasting and Prayer*, Hall Deliverance Foundation, Inc., Phoenix, AZ. 1946.

Hanegraaf, Hank. *Counterfeit Revival*, Word Publishing, Dallas, TX., 1997.

Hickey, Marilyn. *Break the Generation Curse*, Marilyn Hickey Ministries, Denver, 1988.

Hoekema, Anthony A. *The Four Major Cults*, William B. Eerdmans Publishing Co., Grand Rapids, MI., 1970.

Klineman, George. *The Cult That Died*, G.P. Putnam's Sons, New York, 1979.

Layton, Deborah. *Seductive Poison*, Doubleday Publishers, N.Y., 1998.

Martin, Walter. *The Kingdom of Cults*, Bethany House Publishers, Minneapolis, MN., 1997.

Mather, George A. and Nichols, Larry A. eds., *Dictionary of Cults, Sects, Religions and the Occult*, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI. 1993.

McConnell, D.R. *A Different Gospel*, Hendrickson Publishers Inc., Peabody, MA, 1988.

McDowell, Josh and Stewart, Don. *Understanding the Cults*, Here's Life Publishers Inc., San Bernardino, CA., 1982.

McLeod, W. L. *Charismatic or Christian?*, Western Tract Mission, Saskatoon, SK. n.d.





Prince, Derek. *Blessing or Curse You can Choose*, Chosen Books , Grand Rapids, MI , 1990.

Rosell, Garth and Merv. *Shoe-Leather Faith*, Bruce Publishing Co. St. Pauls, Minnesota, 1960.

Ryrie, Charles C. *Basic Theology*, Victor Books, Wheaton, Illinois, 1995.

Sire, James W. *Scripture Twisting Methods of The Cults: Twenty Ways the Cults Misread the Bible.* Intervarsity Press; 1980.

Spittler, Russell P. *Perspectives on the New Pentecostalism*, Baker Book House, Grand Rapids MI. 1976.

Synan, Vinson. *The Holiness-Pentecostal Tradition*, W. B. Eerdmans Publishing Co., Grand Rapids, MI. 1997.

Tan, Paul. *Signs of the Times*, Bible Communications Inc., Garland TX. 1979.

The Learning Company, *Compton's Interactive Encyclopedia*, (CD). TLC, Inc. Copyright © 1997.

Wilhoit, Jim & Ryker, Leland. *Effective Bible Teaching*, Baker Book House, Grand Rapids, MI., 1988.




## አዲስ ሕይወትን የማዳረስ ዘዴ

በትመማ ክፊል ስልታዊ አጻጻፍ ለስምንት ሳምንት የወንጌል ስርጭትና የክትትል ትምህርቶችን የያዘ የቡ··ን ጥናት መጽሐፍ።

1983 ዓ. ም.




## የደኅንነትና ዕድገት ትምህርት

ለአዳዲስ አማኞች የተዘጋጀ የደኅንነትን፥ የክርስቲያናዊ ዕድገትን፥ የቤተ ክርስቲያንን እና የአገልግሎትን ምንነት የያዘ ቀላል የክትትል መጽሐፍ።

1985 ዓ. ም.




## መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች

የመንፈስ ቅዱስን ማንነት፥ የጸጋ ስጦታዎችን፥ በታሪክ ውስጥ የተከሰቱ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴዎችንና ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር የሚታዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ የተቃወሱ ልምምዶችን በሰፊው የዘገበ መጽሐፍ።


1989 ዓ. ም.




## መንፈሳዊው ሰው

በሉዊስ ስፔሪ ሼፈር የተጻፈው *The Spiritual Man* ትርጉም። 1ቆሮ. 2ን መንደርደሪያ በማድረግ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊነትና መንፈሳዊ ሰው ባሕርያት የሚያወሳ መጽሐፍ።

1989 ዓ. ም.



## ትንቢተ ዳንኤል

የትንቢተ ዳንኤል ጥናት መርጃ። ለግል፥ ለቡድን ወይም ለቤተ ሰብ ጥናት መርጃ እንዲሆን በጥያቄና መልስ አቀራረብ ከቀላል ማብራሪያ ጋር የተዘጋጀ።

1995 ዓ. ም.